# አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ፤ ትናንትም ዛሬም ነገም!

ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓመተ ምሕረት
ከሞቱ 143 ዓመት ሆናቸው!

ለ143ኛ ዓመት መታሰቢያ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!
All rights reserved

መጀመሪያ ታተመ ሚያዝያ 2003 ዓም
ሁለተኛ ታተመ ሰኔ 2003 ዓም
ሲያትል ዋሽንግተን
አሜሪካ

Copyright 2011 Amare Afelae Bishaw.
Published by Gugsa Magazine
First edition Apirl 2011
Second edition Juen 2011
Printed in U.S.A

P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

የደራሲው መልእክት ሣጥን ቁጥር
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

ከአማረ አፈለ ብሻው!
Amare Afelae Bishaw



ት ጠበብት ተኸመ ሀብተ ገብርኤል



ነት ሐኪም ዓሥራት ወልደየስ!



ሰፍዩ ረሀማን አልሙባረክፑረ ረውልደቱል አንዋር የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ)የሕይወት ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 133 "ለቢላል ጥሩ ድምፅ ስላለው ለቢላል አዛኑን እንዲነግረው አዘዙት:: ለቢላል ተነገረውና ቢላል አዛን አደረገ" ሲሉ ጽፈዋል:: በእስልምና ሃይማኖት ለጸሎት ተነሡ ብሎ በመጀመሪያ ጥሪ ያደረገውን ሰው እስላሞች ቢላል የሚሉት በላይ ገብረ እግዚአብሔር የተባለውን ኢትዮጵያዊ ነው:: ከዚህ በላይ ያሉትን ሆነ ከዚህ በታች ያሉትን የሃይማኖትና የታሪክ መጻሕፍት የምዘረዝራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያምነው አምላክ ስላለ ለማብራራት ነው::

ዶ/ር መጂድ አሊ ካን ሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ዐፋን (ረ.ዐ) በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 9 "መካ ውስጥ ሕይወት በጣም አስቸጋሪ እየሆነች በመጣችበት ጊዜ ሃድረት ዑስማን )ረ.ዐ) ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር በሐበሻ (አብሲንያ)ውስጥ በጥገኝነት መኖር" ሲሉ ሰፋ አድርገው ዘርዝረው ጽፈዋል::

አንባብያን ኢትዮጵያውያን አንድ የምንኩራበት ታሪክ አለን:: ያም በዓለም ላይ ቅድሚያ የስደተኞችን መብት ያከበረች ኢትዮጵያ በመሆንዋ ነው:: ያውም በሃይማኖት ተሰደው የመጡትን እምነታቸውን ሳትጋፋ ነጻነታቸውን አስከብረው እንዲኖሩ ያደረገች አገር በመሆንዋ ዛሬ ክርስቲያኑ ሆነ እስላሙ፣አረታዊው ሆነ የሕገ ልቦናው አማኝ ሁሉም ሊኮራበት ይችላል::

ምናልባት አንዳንድ አንባብያን ግራ እንዳይጋቡ ለማብራራት "ሕገ ልቦና"ማለት ከአሪት መግባት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያመልከው የነበረ ሃይማኖት ሲሆን ዛሬም በጎንደር ክፍለ ሀገር በጎንደር ዙሪያ አውራጃ እና በጭልጋ አውራጃ የሚገኙት ቅማንቶች ጥቂቶች የሕገ ልቦና አማኝ ናቸው:: በሌሎችም አካባቢዎች የተለያዩ አምልኮቶች ያሉ ሲሆን ሁሉም እግዚአብሔር መኖሩን የሚያበስር ሃይማኖት ነው:: መሳፍንቶች እንኳን ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያዝኑና ሊራሩ ቀርቶ ከአባታቸው ቅምጥ ሳይቀር የወለዱ ነበሩ:: ለምሳሌ የሸዋ መሳፍንት አመሠራረት እንዴት እንደሆነ ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከጻፉት ታሪክ ጥቅስ ልውሰድ::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 359 "ከጎንደር መጥተው በመንዝ



አውራጃ የሚቀመጡ በመዛን አውራጃ የሚቀመጡ ቤዛነ ወልዱ የሚባሉ የቅኔና የመጻሕፍት ሊቅ ነበሩ:: የርሳቸውም የሊቅነት ዝና እስከ አምኃየስ ጆሮ ደርሶ ተሰምቶ ነበርና አምኃየስ ልጃቸውን አስፋ ወሰንን ቅኔ እንዲማሩ ካራት አሽከሮች ጋር ወደ ቤዛነ ወልዱ ላኳቸው:: አስፋ ወሰን መንዝ ሄደው ከኙሁ መምህር ቅኔ ተምረው ካስመረቁ በኋላ ከመንዝ ተነሥተው ወደ አንኮበር ለመምጣት ወደራ (የጎላ ወደራ ማርያም አይደለም) ላይ ሲደርሱ ጊዜ መሸባቸውና የአምኃየስ ቁባት በሆኑት በወይዘሮ አትሞች ቤት አሳድሩኝ ብለው አደሩ::"

"በዚያም ሳሉ አስፋ ወሰን የአምኃየስ ልጅ መሆናቸውን ሴትዮዋም የአምኃየስ ቁባት መሆናቸውን ሳይገላለጡ በሌላውም ወገን የአስፋ ወሰን የወጣትነት ጊዜና የመልካቸው ቁንጅና ለወይዘሮዬቱ ደስ ስላሰኛቸው የአስፋ ወሰንን ጓደኞች እሌላ ቤት አሳድረው ወይዘሮ አትሞችና ወጣት አስፋ ወሰን ባንድነት አደሩ:: በዚህ ባንድ ሌሊት ግንኙነት ሴትዮዋ ፀንሰው በኋላ ወሰን ሰገድን ወለዱ" ሲሉ ጽፈዋል::

ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ስህተቱን በሴትዮይቱ ለማስመሰል ሞክረዋል:: መልሰው ደግሞ አስፋ ወሰን ያወቁ መሆናቸውን አስመልክቶ ገጽ 359 "አስፋ ወሰን የሠሩትን ሥራ ስለሚያውቁትና ሴትዮዋም ያባታቸው ቁባት መሆናቸውን ስለ ሰሙ አባታቸውን ፈርተው ካንኮበር ሸሽተው እንደ መነኩሴ ቆብ ደፍተው ዳባ ደርበው ፍርኩታ ገዳም ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል:: ያም ሆነ ይህ አስፋ ወሰን ከአባታቸው እቁባት ወሰን ሰገድን ወልደዋል:: የወሰን ሰገድ ትውልድ ከቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ዘሩን የሚቆጥረው ትውልድ ነው:: ከአባቱ እቁባት መውለድ ብቻ ሳይሆን አልግባባ በማለታቸው አባትና ልጁም ተዋግተዋል::

የሸዋን መሳፍንት ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ አልፈን ከጎጃም መሳፍንት ስንደርስ ደግሞ በጣም አሳዛኝ የሆነ የግብር ሥርዓት ተጽፎ ይገኛል:: መሳፍንቶች ተደርጎ የማያውቅ ግብር ከሕዝቡ የሰበሰቡ ናቸው:: ዛሬ ይህ ይደረግ ነበር ተብሎ ሲጻፉ ለማመን የሚያስቸግር ተግባር ሲፈጸም ነበር:: ከዚህ በፊት ማንም ነገሥታት አልያም ደግሞ መሳፍንት አድርጎት አያውቅም:: ደጃዝማች ብሩ ጎሹ በጎጃም ሕዝብ ላይ ጥለውት የነበረው ግብር ይህን ይመስላል::

አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፋቸው 98 "ደጃዝማች ብሩ ጉልበት ተሰምቶት ትዕቢት

ሕዝብ ሆይ!ትናትናና ከትናንትና ወዲህ ባሪያ ብቻ ሳይሆን ለሥልጣን ለሹመት ሲባል ሴት ልጅህን ሸጠሃል::"

"በገንዘብ ቀይረሃታል አንተም አንድ ስትሆን ሁለት ሴት ይዘሃል ከእንግዲህ ግን ይህ ቃል ተስተካክሎ በሕግ እስኪጸድቅና እስኪታወጅልህ ድረስ እንድታስብበትና እንድትመርጥ ቀን ሰጥቼሃለሁ:: ነገር ግን ከዚያች ቀን ጀምሮ ባሪያ ተብሎ በግድ ከጌታው ቤት ሲያገለግል የተገኘበት ሴት ልጁ ሳትወድ ተገዳ በክርስቲያን ቤት ሁለተኛ ሚስት ሁና የተገኘችበት ወዮለት::"

"ይሄን ሕግ ልደነግግ የተበላሸውን ሥርዓት ልጠርግ ግዴታየና የመጀመሪያው ዓላማየ ነው:: ይሄንም ላደርግ የሚገባኝና የሚፈጽምልኝ ቅዱስ አምላኬ ነው አሜን ወአሜን" ብለው መናገራቸውን ጽፈዋል::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አጤ ቴዎድሮስ የነበሩአቸውን ቁባቶች አሰናብተው ከእቴጌ ተዋበች አሊ ጋር በሥጋ ወደሙ ተወስነው መኖር ጀመሩ:: አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ብቻ መኖር እንዳለበት ራሳቸው በመጀመራቸው ሌሎች መኳንንቶች ይህን ሕግ ተቀብለው የነበሩአቸውን ቁባቶች ሁሉ አሰናበቱ" ሲሉ አሳማቸውን የነገሡ ቀን የተናገሩትን ከታሪክ ሠነድ አገኘሁ ሲሉ ዘርዝረው ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 8

### አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበት ዓመት መለያየት!

አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ቀንና ዓመት አስመልክቶ የተለያዩ ዓመታት የጠቀሱ ደራስያን ብዙ ናቸው:: ይህን በማስመልከት በዛ ብሎ ዘርዘር ተደርጎ ለመጣፍ ያስፈለገበት ምክንያት አለ:: አንዳንድ ደራስያን ባለማስተዋል ይሁን በግድየለሽነት የጻፉት ትክክል ስላልሆነ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ለማስተካከል ጥረት አድርገዋል::

በእርሳቸው ጥናት መሠረት አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም መሆኑን የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ ጠቅሰው ጽፈዋል:: እኔም እርሳቸው በጀመሩትና እርሳቸው ያላገኙአቸውን የታሪክ



መጻሕፍት በመንተራስ አጤ ቴዎድሮስ የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ነገሡ ብዬ ተቀብዬ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ በማድረግ አቅርቤአለሁ::

<u>ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ</u> ገጽ 14 "የኢትዮጵያ መንግሥት በቀረ በ70 ዓመት ከዚህ በኋላ በነገሡት" ሲሉ ጽፈዋል:: ከ1761 ዓም እስከ 1845 ዓም ድረስ 70 ዓመት ሲቀነስ 70 ዓመት ብቻ አይሆንም:: ስለዚህ የነህ ሰው አጻጻፍ የትኛውን ዓመት መውሰድ እንዳለብን አይገልጽም:: አጤ ኢዮአስ በሻሽ ታንቀው የተገደሉት ግንቦት 8 ቀን በ1761 ዓም ነው::

ታዲያ በኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት የተመሠረተው እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ነው:: በነገራችን ጎንደር ከከተማ የማይወጡ ግንብ ጠባቂ ነገሥታት ሁሌም ነበሩ:: ደጃዝማች ካሳ የማረኳቸው 3ኛው አጤ ዮሐንስ ነበሩ:: ሥልጣኑ የመሳፍንት ነው እንጂ ዘውዱ እኮ ሁሌም ከጎንደር አልተየለም ነበር:: ስለዚህ እኚህ ደራሲ አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ቀን በእኔ እምነት በትክክል አልገለጹም::

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 12 "ንጉሥ በጠፋ በ71 ዘመን እግዚአብሔር ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ:: (የኦሮሞዎች)የጋሎች ግዛት በበጌምድር በጎጃም፤በላስታ በየጁ፤በወሎ ከዚህ ነው ያለቀው" ሲሉ ጽፈዋል::

የደብተራ ዘነብ ከላይኛው ደራሲ ጋር በአንድ ዓመት ይለይ እንጅ የትኛውን ቁጥር እንደያዙት ለእኔ ግልጽ አይደለም:: ከዚህ በታች ደግሞ አቶ ጳውሎስ ኞኞ አመሳክረው በጻፉት ላይ እኔም እርሳቸው ያላገኙአቸውን የታሪክ መጻሕፍት ጨምሬ ለማስረዳት ልሞክር ቅድሚያ ወደ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ትንታኔ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋ ገጽ 78 "ደጃዝማች ካሣ ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በዚያው በየካቲት ወር 1845 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ተብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው ነገሡ፤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ዘመን በደብተራ ዘነብና በአለቃ ወልደ ማርያም በጻፉት ታሪክ በ1847 ዓም ነው ይላሉ:: አለቃ ተክለ ኢየሱስ ግን በ1845 ዓም ነው ብለው ጽፈዋል:: በእነዚህ መጻሕፍት የሁለት ዓመት ልዩነት አለ::"

"እንደነደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደማርያም ዘመን አገላለጽ ከሆነ ቴዎድሮስ የነገሡት 13 ዓመት መሆኑ ነው። አለቃ ታየ አጤ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ነገሡ ስለሚሉ የነገሡበት ዘመን ከአለቃ ተክለ ኢየሱስ ትረካ ጋር ይጋጫል። አቶ መንግሥቱ ለማ የአባታቸውን የአለቃ ለማን ትረካ በጻፉበት መጻሕፍት ትዝታ ውስጥ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነግሠው በ1860 ዓም ሞቱ ይላሉ። ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴም በዝክረ ነገር መጽሐፋቸው በ1845 ዓም ነገሡ ይላሉ። ስለዚህ እኔም አብዛኛዎቹ በተናገሩት በ1845 ዓም ነገሡ ብያለሁ "ሲሉ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጽፈዋል።

እነዚህ 2 ደራሲዎች አጤ ቴዎድሮስ ሲነግሡ በአካባቢው አልነበሩም። ወደ አጤው የመጡት አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን አስገብረው አቤቶ ምኒልክን ይዘው ሲመጡ የመጡ ናቸው። ከእነዚህ ሁለቱ ደራስያን መካከል አለቃ ዘነብ፤የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ የጣፉት አጤው ከሞቱ ከ10 ዓመት በኋላ ነው። ደብተራ ዘነበ የእንግሊዝ ወታደር እስከ ግብጽ መስዷቸው ስለነበር የጻፉትም አሌክሳንደርያ ግብጽ ሁነው ነው።

በዚህ ምክንያት ዘንግተውት ይሆናል እንጂ ደብተራ ዘነብ ሆኑ አለቃ ወልደ ማርያም አጤ ቴዎድሮስን ከመጥላት የተነሣ ታሪክ ለመቀነስ አስበው አይመስለኝም። አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ዘመን አስመልክቶ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ሳያገኙአቸው ከቀሩት ሰነዶች እርሳቸው ካልጠቀሷቸው የታሪክ መጻሕፍት የእርሳቸውን ትረካ የሚደግፉ ሰነዶች እኔም ጅባ ልበል።

1ኛ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ <u>ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 125 "ባጼ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ባጼ ተክለ ጊዮርጊስ 3 ዓመት ባጼ ዮሐንስ 18 ዓመት የቆየችው መንግሥት ከዳዊት ከሰሎሞን ከምኒልክ ገባች" ብለዋል።

2ኛ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ <u>ዋዜማ፤ በማግሥቱ የኢትዮጵያ</u> ነገሥታት የታሪክ በዓል ለማክበር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 "አጤ ቴዎድሮስ 15 ከ1845-1860" ሲሉ ጽፈዋል።



3ኛ <u>የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር</u> በተባለው መጽሐፋ ገጽ 259 "የአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ከ1845-1860 ዓም" ሲሉ ጽፈዋል።

4ኛ በላይ ግደይ <u>የኢትዮጵያ ሥልጣኔ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 175 "ቴዎድሮስ ጀግና ንጉሥ ስለነበር በዚህ የተነሣ ከ1845-1860 ዓም በነበራቸው የ15 ዓመት መንግሥት ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር ተጠቃላ ለመተዳደር አበቃት" ሲሉ ጽፈዋል።

5ኛ በላይ ግደይ <u>ኢትዮጵያ ሀገሬና ትዝታዬ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 150" አጤ ቴዎድሮስ 1845-1860 ዓም በመሳፍንት አገዛዝ ተበታትና የኖረችውን ኢትዮጵያ አንድ አድርገው በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ለማስተዳደር በመጣራቸው ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ ታላቅ መሪ ከመሆናቸው በላይ ጥቅም ሳያስቡና የድሎት ኑሮን ከምንም ሳይቆጥሩት እንደ አንድ ተራ ወታደር ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱ በዋሻና በድንኳን እያደሩ ትውልድን የሚያኮራ ተግባር መፈጸማቸው በታሪክ የተመሰከረ ሐቅ ነው" ይሉና "አክሱም፤ጎንደር፤ ላሊበላ፤ በተባለው መጽሐፋቸውም "ለ15 ዓመት"መንገሣቸውን ጽፈዋል።

6ኛ ብርሃኑ ድንቄ <u>የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 55 "አጤ ቴዎድሮስ በጊዜያቸው የነበሩትን ኃይለኞች ካሸነፉ በኋላ የንጉሥ ተወላጅነት ሳያስፈልጋቸው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ በኃይላቸው ብቻ ተቀዳጅተው የተከፋፈለችውን ግዛት አንድ አድረገው ኢትዮጵያን 15 ዓመት ገዙ"ሲሉ ጽፈዋል።

7ኛ መኮንን አበበ <u>አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍቸው ገጽ 60 "አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነገሡና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር 15 ዓመት ከጣሩ በኋላ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሽጉጣቸውን ጠጥተው አረፉ" ሲሉ ጽፈዋል።

8ኛ አለቃ ኤልያስ ነቢየልዑል <u>የኢትዮጵያ መንግሥት በወርኃ የካቲት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3 "ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም የካቲት 5 ቀን በዕለተ እሑድ ሰሜን በምትገኘው

ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ሲነግሡ ወደ ጎርጎርዮስ ቀመር ስንተረጉመው በ1853 ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ተከብሮ ብሔራዊ ወታደር ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ቁሳቁስ መጤ ነጋዴ ዐረብና ፈረንጅ በነጻ ሳይወስደው በውል ይመሥረት ማለት አገራዊ ፍቅር የተላበሰ ሥልጡን አስተዳደር ነበር። የአገር ልማት እንዲጠነክር በአገር ጠንካራ ማዕከላዊ አስተዳደር ተመሥርቶ ድንቁርና እንዲጠፋ መጣር መልካም ራእይ መሆኑን ማንበብና መረዳት ለሚችል የሰው ልጅ ሁሉ የሚረዳው ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በመንግሥት ደረጃ ብሔራዊ ክብር ያላት መሆንዋን ማሥመራቸው የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው በመረዳታቸው ነው። ይቅርታ አድርጉልኝ ዛሬ ዘመናዊ በሆነ ሃይማኖት በእኛ ቄሶች ድክመት ወደ ሌላ ሃይማኖት የተራመዳችሁ ወገኖቼ ብዙ ናችሁ። በትክክል ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ስሕተት የለባትም። ስህተቱ የበስማም ቄሶች እንጅ የሃይማኖቱ አይደለም። አጤ ቴዎድሮስ ይህ ሃይማኖት ይከበር ብለው በአዋጅ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸው ደካማ ጎኑን የሚችሉትን ያህል አርመዋል።

ቤተ ክህነቱን እንደእርሳቸው ጠንካራ አጤና እንደ አለቃ አካለወልድ ያለ አስተማሪ ሐዋርያ ኑሮ ቢሆን ዛሬ ፕሮቴስታንት በኢትዮጵያ አይጨፍርባትም ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "አንድ ወንድ ላንድ ሴት" ያለውን ከልብ በማመን የነበሩአቸውን ቁባቶች አስወግደው ግንባር ቀደም" ራሳቸው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ሌሎችን በዚህ ተግባር እንዲጠኑ ለማድረግ አዋጅ ማወጃቸው ያስመሰግናቸዋል ዳሩ ግን ጌታችን ካስተማራቸው ሐዋርያት መካከል ይሁዳ በ30 ብር እንደሸጠው ሁሉ የእኛም ቄሶች እነሱ ያላደረጉትን አጤ ቴውድሮስ በማድረጋቸው ጠላት ሆኑአቸው። ከተራ ቁጥር 1-7 ያሉት በዚያን ወቅት ለነበሩት መኳንንቶች የማይዋጥላቸው እንደ መቅሠፍት የሚፈሩአቸው ነበሩ።

"1ኛ ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ፥ እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ እንዲቀመጥ፥ ነገር ግን ክርስቲያን



ከአንድ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፥እስላሙም ከእስልምና ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ሲያስተምር ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪውም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፥ደረቱም በጦር ይወጋል።

2ኛ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው።

3ኛ "ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ መሬት የመንግሥት ይሆናል። ገበሬው መሬት ተሰጥቶት አርሶ ግብር የሚከፈለው ለመንግሥት እንጂ ለካህናት ለደብተራ አይደለም። "የሚለውን አንዳንድ ሠነድ እንዲህ ሲል መዝግቦታል "ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበር ሆኖ ይቆያል" ይላል። ይችን ቄሶች ያስገቧት ሳትሆን አትቀርም።

4ኛ የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች በዕለት ተግባራቸውና በደመወዝ እንዲሠሩ እንጅ ባርያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈጽሙ ሲሸጡና ሲገዙ ቢገኙ እንደነፍሰ ገዳይ በአደባባይ እንዲሰቀሉ ወይም በግዞት እንዲኖሩ።

5ኛ ማንም ሰው ሴት ልጁን ለአቅመ አዳም ሳትደርስ ለሹመትና ለሥልጣን ተብላ እንዳትዳር ይሁን። የቤት ሠራተኞች ገረድና አሽከሮች ለሥራ ከመቀጠራቸው በፊት ደመወዝ እንዲከፈላቸው በውል ማድረግ ይገባቸዋል። ከአሠሪያቸው ጋር ተጣልተው ቢወጡ በውላቸው መሠረት የሠሩበት ገንዘብ ይከፈላቸው።

6ኛ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በየሞያው ተሰማርቶ መተዳደር ይገባዋል። ማንኛውም ሰው በሙያው እንዲሰለፍ ይሁን ሲባል ካህኑ አርሶ ይብላ እንጂ ሞያዬ ቅስና ስለሆነ ሕዝቡ ይቀልበኝ ሊል አይገባውም። ነገር ግን ወታደር በውትድርናው ደመወዙን መንግሥት ይከፍለዋል። ገበሬም በግብርናው፥ነጋዴም በንግዱ በየሞያው ይደር።

7ኛ ገበሬው ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስና ነጋዴ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ግብር እንዲከፍል፤ነገር ግን በትክሻው ተሸክሞ

በአገራቸው ያለውን ጸጥታ ለማስከበር አቻ ለአቻ ወዳጅነት በመፈለጋቸው ነው።

ዶ/ር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ የምዕራባውያን ሥልጣኔና ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ትንተና በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 93 "የአጤ ቴዎድሮስ ፍልስፍና በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ ያለው ነው። አጤ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ መሠረቱንና ውሉን ለመያዝ እንጂ ሙሉ በሙሉ በውጭ ኃይል ሥር መውደቅ እንዳይደለ በተግባር አሳይተዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ የነበሩት ለአገር ግንባታ እንጂ የዛሬዎቹ ባለሥልጣኖች እንደሚያደርጉት የአገርን ክብር ለማስደፈር አልነበረም።

ሜ/ጄኔራል ነጋ ተገኝ የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሠራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 14 "አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማሠልጠንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስተባበርና አንድ ለማድረግ የተጣደፉት ዋናው ምክንያት።"

"በአንድ በኩል በመዘኑ ኢንዱስትሪ የሠለጠኑ አውሮፓውያን እስያንና አፍሪቃን በቅኝ ገዥነት በመቀራመት ላይ ስለነበሩና እንዲሁም ቱርኮች (ኦቶማን ኤምፓየር) ሰሜን አፍሪካን በተለይ የዓባይ ወንዝ ድርጎኛ የሆነችው ግብፅንና ሱዳንን በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉ በኋላ በቀይ ባሕር በተለይ በኢትዮጵያ ድንበሮች ብቅ ጥልቅ ይሉ በነበረበት ወቅት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

የውጭ ግንኙነት ዓላማ ለአንድ አገር አቻ ላቻ የጥቅም ወዳጅነት የሚመሠረት ሲሆን የባሕርና የየብስ ንግድን ሌላም ዳር ደንበርን ማስጠበቅ ይጨምራል። ዳር ደንበር ለማስጠበቅ የአገር ውስጥ ፀጥታን ለማስጠበቅ አቅም ያለው አገር ራሱ የጦር መሣሪያ ያመርታል። አቅም የሌለው መንግሥት ደግሞ በገንዘቡ የሚገዛው ማንነቱን ለማስከበር አስቦ ነው።



ናደው ከበደ ሙዳይ መጽሔት ጥቅምት-ሕዳር 1986 ዓም ገጽ 20 "ከምዕራባውያን ጥበብን በመቅሰም አቅደው የተነሡ የመጀመሪያው ንጉሥ ዳግማዊ ቴዎድሮስ መሆናቸውን በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሷል። እርግጥ ቴዎድሮስ የፈለጉት እደጥበብ በጦር መሣሪያ ጥይት ላይ ያተኮረ መሆኑ አይዘነጋም። ይህም ፍላጎታቸው ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው። ቴዎድሮስ የውስጥ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማንበርከክና የውጭ መሪዎችን ለመቋቋም መሣሪያ ያስፈልጋቸው እንደነበር አያጠራጥርም።"

"እኒያ ከጊዜያቸው ቀድመው አገራቸውና ሕዝባቸው ሳይዘጋጁ አንዷት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የጦር መሣሪያ እደጥበብን በዘዴ ሳይሆን በኃይል ወደአገራቸው ለማስገባት የሞከሩት ቴዎድሮስ የራሳቸው እቅድ መሰናክል ሁኖ ጥሏቸዋል።"

"የቴዎድሮስ ዓላማ በውጭ ወረራና በአገር ውስጥ የወገን ጠላቶቻቸው ደባ ከተጨናገፈ በኋላ አገራችንን ከሥልጣኔ ጎዳና ያስተዋወቋት ዳግማዊ ምኒልክ መሆናቸው አሌ ሊባል የማይችል ሀቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

የውጭ ግንኙነት ለአንድ አገር መንግሥት ዋና ቁልፍ ነው። የምጣኔ ሀብት እርዳታ ሆነ የምክር አገልግሎት የጦር መሣሪያ እርዳታ ሌላም ሌላ ግንኙነት የሚደረገው ቅድሚያ ራሱን አደራጅቶ አንቱ መባል አለበት። በሀገሩ ውስጥ ፀጥታ ማስከበርና አውደልዳይ ወሙኔን ማጥፋት ትውልዱን በአዲስ ሥርዓት ኮትኩቶ አንጾ ማሳደግ ከሌላው አገር ጋር የሚያገናኝ ቋንቋ ማስተማርና ሌላም ሌላ ጉዳይ ይመለከታል።

አጤ ቴዎድሮስ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታት ያልፈጸሙትን እርሳቸው ብዙ ተግባራት ጀምረው ነበር። ከውጭ አገር ጋር የሚያስተረጉሙ ሦስት ቋንቋ የሚናገሩ ለምሳሌ 1ኛ ዐረብኛ፣2ኛ እንግሊዘኛ፣3ኛ ፈረንሳይኛ የሚያስተረጉሙ ባለሞያዎች ነበሩአቸው አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ተግባር አከናውነዋል።

መክፈል ይህም ብቻ አይደለም። መሣሪያም ማምረት አስፈላጊ መሆኑን ከተረዱት በኋላ ነው ለአንዲት ኢትዮጵያ አለኝታ ለመሆን የተነሡ። ቆርጠው የተነሡት ቀደም ብሎ ሲሆን ዋናው ግን ደግሞ ወታደር ደመወዝ መክፈል ብሎም ደግሞ የጦር መሣሪያ ከአገር ውስጥ ማምረት ዋናው ዓላማቸው ነበር። በተለይም ከልጅነት ጀምረው የቱርክን ኃይል ያዩት በመሣሪያ ብልጫና በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የታነጸ በመሆኑ እርሳቸውም ይህን ሲያደርጉ ኢትዮጵያ ስትከበር ታየቻቸው።

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ <u>የአናብስት ምድር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 15"አጤ ቴዎድሮስ ወታደራዊ ስለነበሩና ወታደራዊ ውጥኖቻቸውም ከኃያሏ የቱርክ መንግሥት ጋር ያጋፋኛል ብለው ራሳቸውን ስላሳመኑ፤ወታደሩና ባላገሩ መካከል በምግብና በተመሳሳይ ፍላጎቶች የተነሣ የነበረውን አለመፈቃቀዶች ለማስቀረት ለወታደር ቋሚ ደመወዝ መክፈል ጀምረው ነበር።"

"ጦሩ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚያጋጥመውን የምግብ ችግር ለመቆጣጠር የእህል ጎተራ ሲያቋቁሙ ቱርኮች ምጽዋን ዘግተው ስለነበር ንጉሡ የሚያስፈልጋቸውን የጦር መሣሪያና ጥይት ለማግኘት ስለተቸገሩ ራስን በሀገር የማስታጠቅ ጥረት አደረጉ" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ሁሉ የተደረገው እንግዲህ ጎንደር ደብረታቦር ጋፋት ላይ ነበር።

<u>መይሣው ጋዜጣ</u> ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓም ገጽ 3 "በዘመኑ አብዮት የመራ ሠራዊትን በቋሚ ደመወዝና ማሰረግ የመራ፤ባርነትን የከለከለ፤የመጀመሪያውን የመንገድ ሥራ ያስጀመረ፤አብሮ እየቆፈረም የሠራ ባሕር ኃይል የማቋቋም ዓላማውን በጣና ሐይል ላይ ታንኳ በማሠራት ያሳየ፤ኢትዮጵያ ራሷን ከጠላቶቿ ሁሉ ለመከላከል ጠንካራና የተደራጀ የተማከለ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ያለው በዲሲፕሊን የሚመራ ሠራዊት።"

"እንደሚያስፈልጋት አምኖ ተግባራዊ ለማድረግ ቀን ከሌት የጣረ የማሰነ፤የተንከራተተ ታክስና ግብር ለአገርና ለመንግሥት አስፈላጊ መሆኑን አምኖ የደነገገ ግን ደግሞ መሃይምነትና ድንቁርና በፈነጨባቸው እንቅፋቶች ተግባሩ የተሰናከለ ከድሀው ሕዝብ መካከል መጥቶ እግዚአብሔር ጉልበቱን ብርታቱንና ፅናቱን ሰጥቶት



ጠላቶቹን ሁሉ በጦር ሜዳ ገጥሞ እየረታና እያሸነፈ ስሙና ታሪኩን ለዝንታለም የተከለ። ወታደሩን በደመወዝ የቀጠረ መሪ ቴዎድሮስ ነበር" ሲል ጋዜጣው ጽፏል።

ቀደም ሲል የነበረው የመንግሥት ወታደር ከአርሶ አደሩ ቤት ገብቶ ያገኘውን በልቶ ነበር የሚኖረው እንጂ ደመወዝ አልነበረውም። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተማርሮ ኑሮአል። ምክንያቱም ከቤቱ ሊያድር የመጣው ወታደር "በቂ ምግብ አላበሉኝም" ብሎ መክሰስ ይችል ነበር። መንግሥት "ወታደሬን ያልቀለብክ እኔን በመናቅ ነው"ብሎ አርሶ አደሩን ያሰቃየው ነበር።

አንዳንዱማ ምግብ ብቻ ሳይሆን ሚስትህንም ስጠኝ የሚል ባለጌ ነበር። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የመንግሥትን ወታደር "ተሠሪ" ይለዋል። ይህ ተሠሪ ሕዝቡን ያሰቃየ መሆኑን አጤ ቴዎድሮስ ስለተረዱ ገና ሳይነግሡ ልጅ ካሳ ሲባሉ ጀምሮ ሰዎቻቸው ከሰው ቤት ገብተው አይበሉም ነበር።

"ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ"የሚባለው በእርሳቸው ደርሶ ሲነግሡ ዓላማቸውን በተግባር ለማዋል ሲሉ ቅድሚያ በቤተ ክሕነቱ ተይዞ የነበረው መሬት የመንግሥት መሆኑን አወጁ። አከታትለውም ሕዝቡ ለመንግሥት ግብር ይክፈል እንጂ ወታደር ከቤቱ አይገባበትም ብለው ሲያውጁ በተሠሪ ላይ ጥላቻ የነበረው ሕዝብ አዋጁን በደስታ ተቀብለ።

•
Richard Pankhurst <u>STATE & LAND IN ETHIOPIAN HISTORY</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 93 **Tewodros endeavoured at the same time to establish a regular paid army on modern lines, and soon after his coronation in 1855,introduced payments for his troops, obliging them to pay the peasantry for whatever food they required This great reform** ትርጉም።

"በተመሳሳይ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ደመወዝ የሚከፍለው ዘመናዊ መደበኛ ሠራዊት ለማቋቋም በ1855 ዘውድ እንደጫኑ ወዲያው ለወታደሮቻቸው ክፍያ በመፈጸም ከገበሬው ለሚሰበሰበት ማንኛውንም ምግብ እንዲሰበስቡ በማስገደድ ይሄንን ትልቅ ማሻሻል አደረጉ" ሲሉ ጽፈዋል።

ባሕላዊ ቅሳቁስ የሚያዘጋጁትን ብሉም ቤተ እስራኤላውያን ኢትዮጵያውያን በጋብቻ የተቀላቀሉ መሆናቸውን ሕፃናቱንና ሬዲዮ ጣብያ ያላቸውን እንዲሁም ኳስ ተጨዋቹን ሌሎችንም በተለይም ካህናቱንና የኢትዮጵያውያንን ማኅበራት አስመልክቶ ሰፋ ያለ ማብራሪያ መጽሐፉ ይሰጣል:: ይህን ካልኩኝ በኋላ በእስራኤል አገር ያለው ዴር ሡልጣን ገዳም በቤተ እስራኤላውያን ክንድ ላይ የወደቀ መሆኑ ለማሳሰብ እወዳለሁ::

የእስራኤል መንግሥት የዓረቡን ዓለም በተለይ የግብጽን ጠባይ የሚመረምርበት በዴር ሡልጣን ገዳም ዙሪያ መሆኑ አይዘነጋም:: ስለዚህ ይህን ገዳም ደግሞ ባላቸው ተሰሚነት ኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች ባለጉዳዮች ናቸው:: አንድ መገንዘብ ያለባቸው ታሪክ ቢኖር ደግሞ ይህ ገዳም የኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ርስት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ይሁዲዎችና የኢትዮጵያ እስላሞችም ቅርሱ የክርስቲያኖች ነው ብለው ዝም ሊሉት አይገባም::

በተለይም የዚህ ገዳም ጉዳይ እስራኤል አገር በሚኖሩ ዘራቸው ኢትዮጵያዊ በሆኑት ትከሻ ላይ የወደቀ ነው:: ደግሜ የምለው ዋናው የታሪክ ቅርሳችን የሁላችን መሆኑን ተረዱ እላለሁ:: ታሪክ ሕያው ሁኖ ይኖራል! ለዚህም የዴር ሡልጣን ገዳም በእጃችሁ ያለ መሆኑን አሳስባለሁ:: ይህ ቦታ ከንግሥተ ነገሥታት ሳባ ጀምሮ የኢትዮጵያውያን ርስት ነው::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው <u>ክብረ ነገሥት</u> የተባለው መጽሐፍ ገጽ 13 "አንድ ስሙ ታምሪን የተባለ አስተዋይ የነጋዴዎች አለቃ ነበር:: አምስት መቶ ሃያ ግመሎችንም ይጭን ነበር:: ሰባ ሦስት ያህል መርከቦች ነበሩት:: ያን ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ ይሠራ ዘንድ ወደደ:: ነጋዴዎችም መጥተው ከእሱ ወርቅና ብር እንዲቀበሉና እሱም ከእነሱ ለሥራው የሚያሻውን እንዲቀበል"ሲል ጽፏል::

በዚህ ሰዓት ከሌሎች ነጋዴዎች ተለይተው ታምሪን ዴር ሡልጣን ላይ ዐረፉ:: እርሳቸውም የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ተመልክተው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ ለንግሥተ ነገሥታት ሳባ በመንገራቸው ንግሥተ ነገሥት ሳባም ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ከዚሁ ዴር ሡልጣን



ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ሰፍረውበታል:: ኋላም ልጃቸው ቀዳማዊ ምኒልክ እና ወንድማቸው ዛገ አባታቸውን ሊጠይቁ ሲሄዱ አብረዋቸው የመጡት መኳንንቶችም ከዚሁ ከዛሬው ዴር ሥልጣን ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ለ4 ዓመታት ሰፍረውበታል::

የኦሪት እምነት በኢትዮጵያ ከተሰበከ ጀምሮ በያመቱ ኢትዮጵያውያን ወደ ቅድስት አገር ሲሄዱ የሚያርፉበት ከዚሁ ዴር ሡልጣን ዛሬ ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ሲሆን ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ወዲህ በተለይም በ34 ዓም ግንቦት 8 ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት የተማረኩት ግማሾች ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቦታ ላይ አርፈውበታል:: ከነዚህም አንዱ በሐዋ ሥራ 8 ተጽፎ የምናገኘው ባኮስ ጃንደረባው ያረፉበት ከዚሁ ቦታ ላይ መሆኑ አይዘነጋም:: ስለዚህ ይህ ዴር ሥልጣን ገዳም ከነጋድራስ ታምሪን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ያፈሩበት ነበር::

መኮንን ዘውዴ <u>ኢትዮጵያ እና ኢየሩሳሌም</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 1 "ዴር ሡልጣን ገዳም የሚገኝበት ቦታ ንግሥት ማክዳ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ የታሪክ የባለመብት ርስት የመሠረተችው ከ4490 ዓመተ ዓለም ጀምሮ መሆኑን የታሪክ ማኅደር ያስረዳል::"

"ይህ የታሪካዊ ይዞታ የቃል ኪዳን መሸጋገሪያ በመሆን ብዙዎችን ኢትዮጵያውያንን ከዓለም ክርስቲያኖች ጋር እያገናኘ የቆየ፤ በበለጠ ሲያገናኝ የኖረና የሚኖር ታላቅ መሠረት ስለሆነ በተለይ ኢትዮጵያውያን የንግሥቲቱን ታሪካዊ ምግባር ሲመሰክሩ ኖረዋል፤ ይኖራሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

ስለዚህ በእስራኤል አገር ያላችሁ ኢትዮጵያውያን የኦሪትን ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የምትቀበሉት ታሪኩንም ጭምር መሆን አለበት:: ያ ማለት ደግሞ ዴር ሡልጣን ገዳም የናንተም ርስት በመሆኑ ግብፆችና የዓረብ ተስፋፊዎች ከኢትዮጵያውያን ቀምተው ሊወስዱ እየጣሩ ናቸው:: ታዲያ እናንተ እያላችሁ እንዴት ከኢትዮጵያውያን እጅ ሊወሰድ ይችላል::

አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ቅኝ ግዛት ለማላቀቅ የነበራቸው ምኞት ሳይሳካ ቢቀርም የእርሳቸው ልጆች እነሆ

ትግሬዋ የመቀሌ ተወላጅ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ልጃቸውን አጤ ገላውዴስን ለመርዳት የመጡትን ፖርቱጋሎች በማጠናከር ከፍተኛ ጀብድ የሠሩ ሲሆን በሌላው አንጻር የአጤ ግራኝ አህመድ ባለቤት እቴጌ ድል ወንበራ ጀግና ሴት ነበሩ።

በተለይም ራሱን ችሎ ስለ ሁለቱ እቴጌዎች ጥናት ቢደረግ በድርድር ወይም በፈረንጅ ቋንቋ በዲፕሎማሲ ተግባብተው ልጆቻቸውን እንዴት በእየጃቸው እንዳስገቡ ያስመሰግናቸዋል። ለምሳሌ አጤ አህመድ ግራኝ የማረኩትን ክርስቲያን ለዐረብ ባርያ ይሸጡ ስለነበር የአጤ ልብነ ድንግል ልጅ አቤቶ ሚናስ የኋላው አጤ ሚናስ፣ አቡዘቢብ ለባርነት ተሸጡ።

በአንጻሩ የአጤ ግራኝ አህመድ ልጅ ወገራ በአጤ ገላውዴዎስ እጅ ወደቁ። በዚህ ሰዓት ሁለቱ እቴጌዎች ተላልከው ልጆቻቸውን ተመላልሰዋል። በጎንደር ከተማ ራሱን ችሎ የሚገበኝ ቀስቋም ቤተ ክርስቲያንን ያሠሩት እቴጌ ምንትዋብ የንጉሠ ነገሥት አጤ በካፋ ባለቤት ሲሆኑ ባላቸው ሲሞቱ ከልጃቸው ከአጤ ኢያሱ ጋር ሁነው የኢትዮጵያን መንግሥት ሲመሩ ቆይተዋል።

ኋላም ልጃቸው አጤ ኢያሱ በካፋ ሲሞቱ ከልጃቸው ልጅ ከአጤ ኢዮአስ ጋር ሁነው የአገር መምራቱን ተግባር ተረክበው ሲያስተዳድሩ ኑረዋል። በዚህ ወቅት የአጤ ኢዮአስ እናት እቴጌ ቤርሳቤህ "ዛሬስ የአገር የማስተዳደሩ ተግባር ለእርስዎ ሳይሆን ለእኔ ይገባል ብለው" አማታቸውን ከሥራው አስወግደው እርሳቸው ከወሎ ኦሮሞዎች ቤተሰቦቻቸው ብዙ ጦር አስመጥተው መንግሥት መምራት ጀምረው ነበር።

ምንም እንኳን የዘመነ መሳፍንቱ አስተዳደር ይሁን እንጂ የትንሹ ራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ጀግና መሆናቸውን የሚያሳየው ደጃዝማች ካሣን ለመግጠም ራሳቸው ጦር መርተው የሄዱ ናቸው። የልጃቸው ልጅ የአጤ ቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ተዋበች አሊም ለልጅ ካሣ አንድ የብልት ሥጋ አያታቸው እቴጌ መነን በመላካቸው በመበሳጨት ሲያንቃቁአቸው እንዲህ ብለው ነበር።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 43 "የትግሉ ተካፋይ የሆነችውና የሚወዷት ሚስታቸው ወይዘሮ ተዋበች



በሁኔታው ከርሳቸው ይልቅ አጥብቃ ስለተቆጣች ልክ ካሣ ወደተኛበት ክፍል ገብታ ከአጠገባቸው ቆም ብላ እንዲህ እያለች ታንቃቃቸው ጀመር። ሲሆን መጥኑ ተግበስብሶ በተቀበሉን ነበር? በቀርስ ድልብ ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ ሥጋው በመልከኛ ጠጁ በገንቦኛ በተላከልን ነበር? እንዴት እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተላከልን ከአለች በኋላ በተጨማሪ ጀግኖችን እወዳቸዋለሁ፥ አከብራቸውአለሁ ፥ፈሪዎችን ግን እንቃቸዋለሁ አብሬአቸው ለመኖርም አልፈቅድም፥ የሚል ኃይለ ቃል ታሰማ ጀመር" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር አታካሮ ከገቡ በኋላ ቀሳውስቱ እርሳቸውን ለመጣል ያልተቆጠበ ጥረት አደረጉ። ከሥልጣን ለመጣል ብቻ ሳይሆን አጤውን ለመግደል ሞክረዋል። ካህናቱ አጤ ቴዎድሮስ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ሲቀርቡ መርዝ ጠቅቅለው ሊያቆርቧቸው ሲሉ ነቁባቸውና "በመጀመሪያ አንተ ቁረብና እኔን አቁርበኝ" ብለው ሲያፈጡበት ራሱ ቀምሶ ፍግም ብሏል።

አንድ ወዳጄ በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው "ስሜን አትጥቀስ ካህናቱ በሕይዎት እያለሁ ከኅብረተሰቡ ጋር እንድኖር አያደርጉኝም። ታሪኩን ግን እየተረጎምኩኝ እነግርሃለሁ" ሲሉ ቃል አስገብተውኛል። እኔም ትክክለኛ ስማቸውን አልገልጽም። እርሳቸው በዚህ ስም ተጠቀም ሲሉ በሰጡኝ ስም አሰግድ ድሌ እያልኩኝ እጽፋለሁ። እኔ የሰማሁትን ታሪክ ቄሶችን ፈርቼ ሳልጽፈው አልቀርም።

አቶ አሰግድ ድሌ <u>በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ</u> ያላቸው "አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር እየተካረሩ ስለመጡ እነሱም አልተኙላቸውም። አጤው ከቦታ ቦታ ሲንከራተቱ ደብረታቦር ላይ ካህናቱ እቴጌ ተዋበች ሲቆርቡ መርዝ አቅምሰዋቸው በዚሁ ምክንያት ታመው ሞቱ" ሲሉ ነግረውኛል። አጤ ቴዎድሮስ የአገራቸው ፍቅር እያንገበገባቸው ባለበት ወቅት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች አሊ ነሐሴ 13 ቀን 1850 ዓም ሞቱ። ከፍቅራቸው ብዛት የተነሣ አስከሬን ይዘው እስከ ጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓም አልቀበሩአቸውም ነበር። ሬሳ ተሸክመው አገር ለአገር ሸፍታ ለማደን ይዞሩ ነበር። መቅበራቸው አልቀረምና ከቀበሩ በኋላ ይህን ሲሉ አንጎራጎሩ።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አባባል ከውጭ ውላችሁ ተርባችሁ ከቤት ለመድረስ እየሮጣችሁ ስትመጡ ከጓሮ ስትደርሱ ትንዝ የሚላችሁ ጭቅጭቅ ከሆነ ራባችሁ ትቶአችሁ ይሄዳል:: አንጀታችሁ እጥፍ ብሎ ጭቅጭቅ ፈርታችሁ ጓሮ ለጓሮ ስትዞሩ ታመሻላችሁ:: እውን እንዳይሆን ሕልም ያድርግላችሁ:: ደግነቱ አሁን በምግብ ቤት በልቶ ለምኝታ ይመጣል:: ይህ ደግሞ ያለው በከተማው እንጂ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወንዶች ይህን እድል አያገኙትም::

አጤ ቴዎድሮስ የገጠማቸው ይህ ዓይነት ችግር ነበር:: እርሳቸው በእቴጌ ተዋበች የለመዱት ከቤት ሲገቡ ቀን የዋሉበትን ጭቅጭቅ የሚረሱበት ደስታ እንጂ ሌላ ጭቅጭቅ የለባቸውም ነበር:: እቴጌ ጥሩወርቅ ግን ካልተጨቃጨቁ ምግብ የማያቀርቡ ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት የሚወዱአቸው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ ከሞቱ በኋላ እቴጌ ጥሩወርቅን ከአገቡ ወዲህ ነው:: እኒህ እቴጌ ጥሩወርቅ ጠባያቸው አስቸጋሪና አናዳጅ ሆኑባቸው:: እንኳን አሜሪካና አውሮፓ ኢትዮጵያ ያላችሁም ብትሆኑ ርእሰ ብሔር ክሊንተን ከወይዘሪት ሞኒካ ጋር መማገጣቸውን በተመለከተ በዓለም ጋዜጠኞችና ቀላጆች ተውኔት መጫወቻ ሁነው ነበር:: በዚህ ወቅት ወይዘሮ ሔላሪ ክሊንተን ስለ ባለቤታቸው ምንም ዓይነት ቅይምታ ሳያሳዩ ቀርተዋል:: በዚህ ምክንያት ርእሰ ብሔሩን የሚጠሉ ሰዎች ያሉ ቢሉም ከሥልጣናቸው ሳይወርዱ ቀናቸውን ጨርሰው ለቀዋል::

በዚህ ወቅት ባለቤታቸው ከሕዝብ መገናኛውና ከሪፓፐሊካኑ ጋር ቁመው ቢሆን ኑሮ ርእሰ ብሔሩ የቀራቸውን ዓመት አይጨርሱም ነበር:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ወይዘሮ ሔለሪ ወይም (ፈርስት ሌዲ) አስተዋይ በመሆናቸው ነው:: አንባብያን ልብ በሉ በተለይ ትዳር ያላችሁ ሁሉ ከሥራ ውላችሁ ከቤት ስትገቡ በትዳራችሁ ውስጥ ያለው መልካም ገጽታ ከሆነ እናንተም ቀን ተበሳጭታችሁ ብትውሉ እንኳን ከቤት ስትገቡ የሚጠብቃችሁ ጉምጉምታ የዓይን ግልምጫ ከሆነ እንቅልፍ ሳትተኙ ታድሩና ጧዋት ሥራ ስትገቡ ምን ዓይነት ስሜት እንዳላችሁ በራሳችሁ ታዘቡ:: ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአበው ንግግር ልውሰዳችሁና "ከቤቱ በታች አቀበት ያለበት ሰውና ተጨቃጫቂ ሚስት ያለው ሰው አንድ ናቸው" ይላሉ::



# ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት!

"ይሉኛል ይልኛል ጨካኝ
ሀሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ"
ይሉ ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ በገና ሲደረድሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ከመጨከናቸው በፊት የምሕረት አዋጅ ያወጣሉ:: ከዚያም ምሕረት ማድረጋቸውን ያስነግራሉ:: የተናቀውንና የተጠላውን ሥራ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሁነው ይሠራሉ:: ዶማና መጥረቢያ ይዘው መንገድ ሲሠሩ ይውላሉ::

የወጣውን አዋጅ ቅድሚያ ራሳቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ከዚያም ወታደሩና የመንግሥት ሠራተኛው ተግባራዊ እንዲያደርግ ያዛሉ:: ለምሳሌ ቁባቶቻቸውን ትተው ከእቴጌ ተዋበች ጋር በሥጋ ወደሙ እንደተወሰኑት ዓይነት ማንኛውንም ራሳቸው ቅድሚያ ያደርጋሉ:: ሌላው ቀርቶ መንገድ ሥራ ሳይቀር እርሳቸው ተሰልፈው ሠርተዋል::

ኢትዮጵያና ዕድሏ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 120 "የብረታ ብረት ሥራ፣የእጅ ሙያ ሁሉ በኢትዮጵያ ልምድ እንደነውር ይቆጠር ስለነበር ቴዎድሮስ ያንን መጥፎ ልምድ ሰብረው እራሳቸው እንደ አንድ ወዛደር ዶማና መዶሻ ይዘው ሙሉ ቀን ከሕዝቡ ጋር በመቆፈርና በመቀጥቀጥ የመጀመሪያውን ዘመናዊ መንገድ በኢትዮጵያ ያሠሩ እሳቸው ናቸው::"

"ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የመንገድ ሥራ አልተለመደም ነበር በማለት አገር ጎብኚ የነበሩት አቶ ኤሚል ዮንቮ የተሰኙት ፈረንሳዊ ሲመሰክሩ የቴዎድሮስ እስረኛ የነበሩት ዶ/ር (አቶ) ሄንሪ ደግሞ ቴዎድሮስ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሆነው ጀንበር ወጥታ እስክትጠልቅ ድረስ ድንጋይ በመሸከም መሬት በመደልደል ይሠሩ ስለነበሩ ሕዝቡም ምግብና መጠጥ ሳያምረው ሙሉ ቀን ሲሠራ ይውል ነበር

ራብ ይግደለው ሲሉ ተቀብለው አሰረው መቅደላ ገቡ በማግሥቱ ዓርብ አምጡ ብለው መነኩሴውን ፈትተው ሰደዱ" ሲሉ ጽፈዋል። የዚህ ዓይነት አሚኪሳ ሞለቶባቸው ነው የጨከኑት።

<u>ኢትዮጵያ ዕድሏ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 121 "ጥረታቸው ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ያልሆነበርን ምክንያት አንድ አቶ ቴዎፍሎስ ዋልድ ማዩር የተሰኘ የስዊስ ተወላጅ ሚሲዮናዊ ባቀረቡት ገለጻ ÷ ቴዎድሮስ እንደገለጹት ይሉና የሥራ ጓደኞቻቸው ያልሰለጠኑ ያልተማሩ ደደቦች እንደ እህያ የታወሩ ስለሆኑ ችሎታ ያላቸው የውጭ አገር የእደጥበብ ባለሙያዎች እንዲላኩላቸው ለአውሮፓ መንግሥታት ጥያቄ አቅርበው ነበር ብለዋል÷ ጥያቄያቸው መልስ ባለማግኘቱ ተቆጥተው በውጭ አገር ዜጎች ላይ የወሰዱት እርምጃ የውጭ ፖለቲካቸውን አበላሸባቸው።"

"እሳቸውም ፈረንጆቹን እንዲጠሉ ካደረጋቸው ነገር አንዱ አቶ እስተርን የተባለ እንግሊዛዊ ሚሲዮናዊ በአውሮፓ አቆጣጠር በ1862 ዓም ሉንደን ባሳተመው መጽሐፍ ቴዎድሮስን በማናናቅ የቴዎድሮስ እናት መንገድ ላይ ተቀምጣ ኮሶ ትሸጥ ስለነበር የቴዎድሮስን ስሙ ልጅ ኮሶ ነበረ። ልጅ ኮሶ ማለትም ትል የሚያጠፋ መድኃኒት ማለት ነው ብሎ ከጻፈ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በመግባቱ አቶ እስተርን ተይዞ ከተገረፈ በኋላ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 3

## አጤ ቴዎድሮስ ሕግ በጣሱት ላይ ጨክነዋል!

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ባሳተመው ገጽ 26 "በግንቦት ገረገራ ላይ ዋግሹም ገብረመድኅን ቢትወደድ ብሩ አባጫት ተጎጃም ተያዙ። ደግሞ እሰኔ ደረስን ጎለም ወልደሚካኤልን ማሩ ሰሎሞንን ደግሞ 4 ሰዎች እነዚህን ዘጠኝ ረጅም ግራር ከሚባለው ሰቀሉአዋቸው እጅ እግራቸውን ቆርጠው በፍትሐ ነገሥት በፍርድ ዋግሹም ገብረመድኅን ንጉሡ ከራስ አሊ በተዋጉ ጊዜ ቆስለው ነበር። ከራስ ጋር ሁነው ሳሉ ንጉሥም አይዞዎ ብለው መቶ ነፍጥ ሰጥተው አገራቸውን አገውን ሹመው ሰደዋቸው ከሸዋ በተመለሱ ጊዜ ነው



አገራቸውን የሰደዱአቸው ከዚያ ከዱ። እግዚአብሔርም ከዳታቸውን አይቶ ከንጉሡ እጅ ጣላቸው ከረጅም ግራር ሰቀሉአቸው" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ዋግሹም ገብረ መድኅን ማለት የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ናቸው። ቅድሚያ ከራስ አሊ ጋር ሁነው አጤ ቴዎድሮስን ወግተው ቆስለው ተማርከው ነበር። ከዚያም ግዛታቸው ተፈቅዶላቸው ተሸልመው ከተመለሱ በኋላ ሸፈቱና ሲማረኩ ተገደሉ። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መጽሐፍ በተለያዩ ገጾች ላይ ገና ደጃዝማች ሳሉ ጀምሮ ቃል ያፈረሰውንና የወጣውን አዋጅ የጣሰውን መግደላቸውን እየደጋገሙ ጽፈዋል።

<u>ስማቸው ያልታወቀ የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት</u> ደራሲ በ55 ገጽ መጣጥፋቸው ውስጥ ገጽ 14-15-25-ማወጃቸውን ጽፈዋል። አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ አዋጅ ማወጃቸውንና እርሳቸው ቃል ለመጠበቅ ሲሞክሩ ሕዝቡ ሊሰማ ቀርቶ እንዲያውም ለሌብነት ተደራጅቶ መጣ። አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የሆነውን ዘውድ ጭነው አንዲት ኢትዮጵያ አንድ አመራር ብለው ገበሬ በግብርናው ነጋዴም በንግዱ÷ሁሉም እንደ ችሎታው በየሞያው ተሰማርቶ በሰላም ይኑር ብለው አወጁ። በዘመነ መሳፍንት ሥር የሰደደው ሌብነት ሞያ ሆኗልና እንዲያውም ሌቦች ተሰባስበው መጥተው ጃንሆይ ሁሉም በየሞያው ሠርቶ ይኑር ካሉ የኛ ሞያ ሌብነት ነውና ይፍቀዱልን ብለው አመለከቱ።

አጤ ቴዎድሮስ በኋላ የሚያደርጉትን እናንተማ ለግል አሽከርነት የምትጠቅሙኝ ናችሁ እናንተ ብቻ አትበቁም ሂዱና እንደናንተ የመሰሉትን ሰብስባችሁ ተመልሳችሁ ኑ። ግን በሌብነት ሞያ ያላስመሰከረ ከሆነ ይዛችሁ እንዳትመጡ ብለው መለሷቸው። ሌቦቹ መሰሎቻቸውን ሰብስበው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ቀርበው ይኸው መጥተናል ሜዳውን ሞልተውታል ብለው አመለከቱ። አጤ ቴዎድሮስም በል ፍጅልኝ ብለው አስፈጇቸው። አቶ ገሪማ ታፈረ ጥፋቱ የሕዝብ ነው ብለዋል።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 169 "በአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመው የወንጀለኞች ቅጣት ሲመዛዘን ጥፋቱ የሕዝቡ እንደነበር የአፈጻጸሙ ዝርዝር ሁኔታ

ያስረዳል። በታሪኩ አቀራረብ እንደተገለጸው አገሌ የአካል ቅጣት ተፈጸመበት ወይም ታሠረ፣ተገረፈ ሲባል ከኃጢአት ንጹሕ ነበርኩ ወይም ጥፋት ሳይገኝብኝ ነው የተቀጣሁ ከኃጢአት ንጹሕ ነኝ ሲል እንደ ጲላጦስ እጁን የታጠበ አይታይበትም ብቻ የተቀጡት አማፅያን ጥፋታቸውን አምነው ምሕረት ጠያቂዎች ሁነው ተገኝተዋል። እንግዲህ ከዚህ ላይ ጥፋቱ የሕዝቡ እንደነበር ማገመዛዘንና መመራመር የሕሊና ዳኝነት አስፈልጎታል" ይሉና።

170 "አጤ ቴዎድሮስ ከእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የሚፈልጉት ገጸ በረከት ታማኝነትንና ተገዥነትን ብቻ እንጅ በሌላው በኩል መብቱ ተጠብቆለት ሀብቱ ተጠብቆ የኑሮ ደረጃውን በሥራ ኃይል እያጠነከረ ወደ አዲስ ሕይወት እንዲመራላቸው በበለጠ ይመኙለት እንደነበር የተጀመረው የሥራ ውጥንና ንድፍ ምስክርነቱን አሳይቷል" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ ከፍ ብሎ የተነበበው ጥቅስ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ የገደሉት በፍርድ ነው እያሉ ነው። የእኔ እምነት ሕዝቡ ለብዙ ዘመናት ሕግ አልባ የሽፍቶች ኃይል በዝቶ በመኖሩ የእርሳቸውን ሕግ ሊያከብርላቸው ባለመቻሉና ሌላው ደግሞ የካህናቱ ቀስቃሽነት በሕዝቡ መሀል ገብቶ አጣልቷቸዋል።

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 243 "ነገር ግን አጤ ቴዎድሮስ ዘመኑ መሳፍንትትን በማስወገድ የባርያ አገዛዝን ሲሽሩ፣የካህናትን ቁጥር ሲወስኑ መሬት የመንግሥት ነው ብለው በዚያ ባለጉልተኛ በሰፈነበት ዘመን ማወጃቸው የሚያስመሰግን ሲሆን ከአካባቢው የተነሣባቸው ተቃውሞ በጎ ሐሣባቸውን ከፍጻሜ ለማድረስ አላስቻላቸውም። ስለዚህ ሐሣባቸውን አልቀበልም ባለው ወገን ላይ ቁርጠኛ እርምጃ ለመውሰድ አስገድዷቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ ሰውን እንደከብት ይሸጥ የነበረ ምድረ መኳንንትና ካህናት ጥቅማቸው በመነካቱ ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ተነሡ። እርሳቸውም ተደጋግሞ እንደተገለጸው ያወጡትን አዋጅ ለመተግበር ስለፈለጉ ሕጉን የጣሱትን ፍትሐ ነገሥት እየተነበበ በጥፋታቸው ቅጣታቸውን ተቀብለዋል።



አታ`ሽልቲ ሐጎስ <u>ሐቅ ሐቂን ለሕፃናት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 115 "ስለ አጤ ቴዎድሮስ ጭካኔ የሚቀርቡት መላምቶች በሙሉ መሠረት የሌላቸው ምክንያቶች ናቸው። ይህ ሁሉ መላምት መምጣትና እንደ ምክንያት መመርመር የሚችለው አጤ ቴዎድሮስ ከመጀመሪያው አነሣሣቸው በርኅራኄአቸው የሚታወቁ ቢሆኑ እንደ ምክንያት ሊቀርብ ይችል ነበር። ጭካኔ የጀመሩት የሆን የሚያስጨክን ገጥሞአቸው ከዛ በሁዋላ የተዳበላቸው ሳይሆን አንድ ብለው ሽፍትነት ሲጀምሩ ጨካኝነታቸው ጎልቶ ይታይ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

አዎ ልክ ነው አጤ ቴዎድሮስ ጨክነዋል ብዙ ሰው ገድለዋል። እጅ እግሩን ቆርጠዋል! ብዙም ሰው ቤት ውስጥ ዘግተው በእሳት አቃጥለዋል። እኔ አጤ ቴዎድሮስ መጨከናቸውን ደብቄ አላውቅም። ነገር ግን ብዙ ኢትዮጵያውያን አጤ ቴዎድሮስ ጨካኝ ናቸው ይላሉ እንጂ የጨከኑበትን ምክንያት ዘርዝረው አያቀርቡም።

አጤ ቴዎድሮስ ለምን ሰውን እጅና እግሩን ቆረጡ? ለምን ቤት ዘግተው በእሳት አቃጠሉ?ለምን ጨከኑ ብሎ የሚጠይቅ የለም ማለት ይቻላል። ብዙ ሰዎች ሲጽፉ እያለሁ መልካም ተግባራቸውን ሳይገልጡ የሚያተኩሩ ከተገደሉት ላይ ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች አንድን መንግሥት ሲጠሉት የሠራውን ሁሉ ይክዳሉ። ይህ ሊሆን አይችልም በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሥልጣን የነበራቸው ግለሰብ ከ200 ገጽ በላይ ክፋታቸውን ሲዘረዝሩ መልካም ሥራቸው 2 ገጽ ብቻ ሁኖ ሳነበው ገረመኝ። ይህን ታሪክ ለመለወጥ የታሪክ ትክክለኝነትን የሚመረምር አብዮት መነሣት ያለበት ይመስለኛል። የአንድን ግለሰብ ታሪክ በታሪክነቱ መልካም ተግባሩ በመልካምነቱ መጥፎው ተግባሩ በመጥፎውነቱ እውነቱን ይዞ ከተቀመጠ ጥሩ ይሆናል። የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ በ2 ተከፍሎ ይጻፋል።

1ኛ መልካም ተግባራቸውን ደብቆ መጥፎ ተግባራቸውን አብዝቶ የሚጽፈው ኃይል አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት ሳሉ ጀምሮ ያለ ሲሆን ዛሬ ያነን በመያዝ ትውልዱን ለማሳሳት ጥረት እየተደረገ ነው።

አንዴ አንድ ነጋዴ ካደረበት አሆችን ሲጭን አንዱን ከረጢት ይረሰዋል:: ይህ ከረጢት 3 መቶ ብር ሲሆን አንድ መንገደኛ አግኝቶ ይወስደዋል። ያ ነጋዴ ብሩ መጥፋቱ ትዝ ሲለው ቤተ ክርስቲያን ሂዶ 300 ብር ስለጠፋኝ ሳገኝልኝ ሰው አንድ መቶ ብር እሰጠዋለሁ" ብሎ ይናገራል:: ገንዘቡን ያገኘው ሰው ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበረው በመሆኑ "እኔ ነኝ ያገኘሁት" ብሎ ሲወስድለት ያ ነጋዴ "የጠፋኝ አንድ ሺህ ብር ነው" ብሎ ከአጤ ቴዎድሮስ ክሶ ይወስደዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ከሳሹን ከሰሙ በኋላ "ቤተ ክርስቲያን ጠፋኝ ብለህ የለፈፍከው ስንት ብለህ ነው" ብለው ሲጠይቁት ነጋዴው፣ "ቅድሚያ ገንዘቤን ያገኘውን ሰው ለማወቅ ስል 300 ብር ብዬ ነው" ብሎ ሲነግራቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ፍርድ ሲሰጡ "ወንድሜ አንተ የጠፋህ አንድ ሺህ ብር ስለሆነ ያንተን ገንዘብ ያገኘው ሰው እስኪመጣ ድረስ ጠብቅ፣ አንተም ሐቀኛ ሰው ያገኘኸውን 300 ብር ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ" ብለው ፈረዱ::

<u>ምኒልክ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥቅምት 1992 ዓም ገጽ 40 "አጤ ቴዎድሮስ ተዚያ ሁሉ ለጋስነታቸው ለዚህ ሸፋጭ ነጋዴ ሺህ ብር እንዲያ ጠፍቶኛል ሲል አንድ 40 ጅራፍ እንደልማዳቸው ሳይረግቡት መስደዳቸው ጉድ አደረጉ" ሲል ጽፏል::

ለነገሩ ጅራፍ መቅመስስ ነበረበት:: መጽሔቱ የፈረደው ትክክል ነበር:: አጤ ሌላም ፍርድ ፈርደዋል:: አንዲት ድሃ ሴት አንድ በጣም የሚያምር ወይፈን ነበራት:: ታዲያ ጎረቤቶቿን "እባካችሁ ቀጥቅጡልኝ" ብላ ብትለምናቸው የእነሱ ላሞች አውራ እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ "ነገ ዛሬ" እያሉ እንቢ ብለዋት ሳለ ይህ ወይፈን በጣም ትልቅ አውራ ይሆንና አንዴ በተራራ ላይ ከብቱ ተሰማርቶ ሣር በሚበላበት ወግቶ ብዙ ከብት ገደል አስገባቸው:: በዚህ ወቅት እነዚህ የላሞቻቸው አውራ እንዲሆን ነገ ዛሬ እያሉ እምቢ ያሉት አርሶ አደሮች ሂደው ከአጤ ቴዎድሮስ ሴቷን ከሰሱ::

አጤ ቴዎድሮስ ተከሳሿን ሴት አቅርበው "ተናካሽ ውሻህን ተቆጣ በሬህን እሰር" የሚል ሕግ መኖሩን እያወቅሽ ለምን አውራ በሬሽን አልጠበቅሽም" ብለው ጠየቋት:: እርሷም ቀደም እኔ ዛሬ የከሰሱኝን



ጎረቤቶቼን እባካችሁ አዳብሩልኝ በማለት ለምኛቸው ነበር:: ነገር ግን እነሱ የላሞቻቸው አውራ እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ እምቢ አሉኝ:: ታዲያ የላሞቻቸው አውራ ሲሆን ለምን አልከሰሱኝም" ስትላቸው አጤ ቴዎድሮስ" የአውራሽን ጥጆች ታውቂያቸዋለሽን" ብለው ቢጠይቋት "አውቃቸዋለሁ" ብላ መለሰችላቸው:: እርሳቸውም "በይ ከከብቶቻቸው መሐል ገብተሽ የአንችን አውራ የመሰሉትን እየመረጥሽ ውሰጅ" ብለው ፈረዱላት:: አተርፍ ባይ አጉዳይ ሁነው ሌሎች ከሰሩ::

አንድ ድሃ ሰው ብዙ ልጆች አሉት:: በዚህ ወቅት ባለቤቱ ትሞትበታለች:: ታዲያ ይህ ሰው ያለው አንድ በሬ ነው:: በዚህ ወቅት የነፍስ አባቱ "የባለቤትህን ተስካር አውጣ"ብሎ ደጋግሞ ይመክረዋል:: ያ ድሃ ሰው ደግሞ ልጆቼን በምን ላሳድጋቸው ብሎ ቢማፀን ቄሱ አልሰማ ይላል:: ይህ ድሀ ሰው ሲጨንቀው ወደ አጤ ቴዎድሮስ ይሄድና የሆነውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገራቸው:: በዚህ ወቅት እርሳቸው ይህን ቄስ አስጠርተው በል "ለዚህ ድሃ ሰው እስር ማድጋ እህል ሁለት በሬ ቅቤም ሆነ እህል ስጠውና የባለቤቱን ተስካር ያውጣ" ብለው አዘዙት::

ይህ ቄስም ምርጫ ስለሌለው የድሃውን ሰው ሚስት ተስካር በራሱ ገንዘብ እንዲያወጣ አድርገውታል:: አንድ ሌባ ሲሰርቅ ይሰማና ባለቤቱ ሊይዘው ሲሞክር ሩጦ አመለጠው:: ነገር ግን "በቴዎድሮስ አምላክ ቁም" ሲለው ይቆማል:: ቀሞ ሲገኝ ሌባውን በጦር ወግቶ ይጥለዋል:: ያ የተወጋ ሰው ወጊውን ካጤ ቴዎድሮስ ፊት በሕግ አቀረበው:: ከሳሹ ሌላው ሰው ማለት ነው::

<u>ምኒልክ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥቅምት 1992 ዓም ገጽ 40 "እግዚአብሔር ያሳይዎ ጃንሆይ!አለ:: አጤ ቴዎድሮስ ግን ይሄን ሁሉ ነገር ዝም ብለው አድምጠው በመጨረሻ በጨለማ ተሰው በረት ገብቶ ከብት የሚወስድ ጅብ እንጂ ሰው አይደለም:: አሁን ጅብ ለምን ወጋ ብለህ ነው መክሰስህ? አበጀ እንኳን ወጋህ!አሉና ተቆጡት:: ወዲያውም ወጊውን ዘወር አሉና ነገሩን የዋጡለት አስመስለው አንተስ ከሳሽ የተናገረው ሁሉ የእውነት ነውን? ብለው እየሳቁ ጠየቁት::"

ሲያደርጉ መሐሪ መሆናቸውን ከአንደበታቸውና ከተግባራቸው በጥንቃቄ ተመልክቻለሁ" ይሉና

ገጽ 27 "ከመጠን በላይ ለጋስና ከማናቸውም ፍቅረ ንዋይ የጸዱ ናቸው:: ለወታደሮቻቸው የጦር መሣሪያ እንደማግኘት የሚያስደስታቸው አንዳችም ነገር የለም:: እስከ ዛሬ ድረስ ድል ያደረጓቸውን ሁሉ ከመማረካቸውም በላይ እንደ ጠላት ሳይሆን እንደ ወዳጅ ያዩአቸዋል:: የእምነታቸው ጽኑነት የሚደንቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ነጋ ወልደ ሥላሴ <u>ባለታሪክ ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 175 "ቴዎድሮስ በዚህ በነገሡበት ወቅት ታላቅ ዝናን አግኝተው ነበሩ:: ቂም የማይይዙ ይቅር ባይ በተለይም ያሸነፏቸውን ጠላቶቻቸውን መሐሪ ጽኑ የሃይማኖት እማኒነት የሠፈረባቸው ንጉሥ ነበሩ:: የዕውቀትና የትምህርት ፍቅር ያደረባቸውና አብረዋቸው ከነበሩ ሰዎች ሁሉ በማናቸውም ረገድ የላቁና ለአስተዳደርም ልዩ ተሰጥዎ የነበራቸው በመሆናቸው ሰዎች የሚያደንቋቸውና የሚከተሏቸው ነበሩ:: እንዲሁም ልዩ ቁመና የነበራቸው ሲራመዱም እንደ ደቦል አንበሳ የንጉሥ አረማመድ የሚራመዱ ማናቸውም ዓይነት ድካም የማይበግራቸው ሰው ነበሩ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ማታ ማታ አንዳንዴ ብቻቸውን በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ወይም ሁለት ወታደር አስከትለው ሰፈር ለሰፈር ይገቡና የሚባለውን ሲሰሙ ያመሻሉ::

<u>ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፈው</u> ገጽ 17 "አንድ ቀን የሚያምኑትን ዘበኛ ይዘው አልባሌ መስለው አዳፋ ጋቢ መሳይ ለበሱና ከጨለመ በኋላ በሰፈሩ ይዞሩ ጀመር:: በየጎጆውም እየተጠጉ ያዳምጡ ነበር:: እኩሉ ያልተኛ እኩሉም ተኝቶ ከዝያ ወድያ ካንድ ወታደር ጎጆ ተጠግተው ቢያዳምጡ ባልና ምሽት በግብረ ሥጋ ሲጣሉ ሰሙ:: ወንድ ይለምናል ሴቲቱም አይሆንም ትላለች::"

"ከዝያ ወድያ ወንድየው በማርያም እያለ ቢለምን በጻድቃን፣በቅዱሳን እያለ ቢቀባጥር እምቢ አለችውና በይ በቴዎድሮስ ሞት እንድትሰጭኝ አላት:: እሷዋም ቴዎድሮስ ከሚሞት ጎንደር አይታረስም አለችና ሰጠችው" ሲሉ ጽፈዋል::



ጥቅሱን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ሳሳጥረውና ጥዋት ባልና ሚስቱ ተጠርተው ከአጤው ሲቀርቡ ጥፋት አጥፍተናል ብለው ሲፈሩ ሽልማት ተሸልመዋል:: አንዴ ደግሞ ጎጃም ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ለማደን ዘምተው ሳለ ማታ ብቻቸውን ያደረጉት ይህን ነው::

<u>ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን</u> ታሪክ የጻፉት ገጽ 18 "አጤ ቴዎድሮስ ብቻቸውን አንድ ወታደር መስለው አዳፋ ልብስ ለብሰው ሆኑራቸው ሽርቤው እንደ ተንጨበረረ ጨሬያቸው በትከሻቸው እንዳደረጉ ከአንዲት ባላገር ሴት ቤት ገቡና እንዴት ዋልሽ አልዋት እሷም እግዜር ይመስገን እንዴት ውልሃል አለቻቸው::"

"መልሰው እባክሽ ርቦኛልና እንጀራ ስጭኝ አልዋት:: እሷም የማነህ ወታደር አለቻቸው፣የተድላ ጓሉ እንጂ የማን ብለሽኝ አልዋት ይህን ተነጋገሩና እንጀራ በርጎ አቀረበችላቸው፡ ውሃም አስታጠበችና መብላት ሲጀምሩ ተቀመጠች:: ከዝያ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ብለው ጠየቁዋት፤ ያ እብድ ንጉሥ ወዴት ደረሰ ይባላል ወሬውን አልሰማችሁም?"

"አልዋት እርስዋም መለሰችና እብዶችስ የተድላ ጓሉ ወታደሮች ናችሁ እንጅ የተቀባ ንጉሥ እብድ አይባልም አለችና መልሳም አሁን ሸዋ ሂዶ ብትሰሙ አገር ስለማጥፋት ደስ ብሏችኋል ያእብድ የምትሉት ንጉሥ ቢዘልቅባችሁ ደግሞ ድምባችሁን አጥፍታችሁ ከአምባ ለመሸሽግ ነው አለቻቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

እርሳቸው የተቆጡ መስለው የቀረበውን ምግብ ሳይበሉት ወደ ሠራዊታቸው ተመለሱ:: ጥዋት ያች ሴት ተጠርታ ተጠየቀች የሆነውን ሁሉ ተናገረች የአካባቢው ቤት በእሳት ሲለበለብ የእርሷ ቤት ሳይበላባትና ሳይዘረፍባት ቀርቶ ሌላም መጠወሪያ ተቀብላለች::

አንዴ አጤ ቴዎድሮስ መንገድ ሲሄዱ ብዙ ልጆች የነበሩአቸው ገበሬ አገኙ:: ስንት ልጅ አለህ ሲሉት 10 አላቸው እርሳቸውም በየዓመቱ ነው የምትወልደው ሲሉት አርሶ አደሩ" ጃንሆይ መንታ መንታ እየሆኑ ነው የተወለዱት አላቸው እርሳቸውም ታዲያ በሬ አለህን ሲሉት የለኝም ቆፍሬ ነው የማሳድጋቸው ሲላቸው ሁለት በሬ ሰጡት:: ይህን ሁለት በሬ መቀበል የሰማ የ16 ልጆች አባት አርሶ

አደር እየተከተለ ይመጣና ጃንሆይ 16 ልጆች አሉኝ በሬ የለኝም ሲሳቸው አራት በሬዎች ሰጡት። ባመቱ በዚያ ሰፈር ሲያልፉ ሁለት በሬ የተቀበለው ገበሬ ጓሮው ጎተራ በጎተራ ሁኖ በሬዎች ከስተው ውሻው ወፍሮ ልጆች አለምልመው ተመለከቱ።

16 ልጅ የነበረው 4 በሬ የተቀበለው ገበሬ በሬዎች ወፍረው ውሻዎች ከስተው ልጆቹ አመድ ወርሷቸው ተመለከቱና "በል አንተ ይዞ ሟች እነዚህን በሬዎች ለዚህ ለሚያርሰው አስረክብ አንተ በእርሱ ታዘዝና እደር። ልጆችህ ከሚራቡ ይህ ጠንካራው ገበሬ አርሶ ያብላቸው ምናልባት ያንተ ልጆች ከዚህ ገበሬ ጥንክርና ሊማሩ ይችሉ ይሆናል" በማለት ቀምተው ለጠንካራው ገበሬ ሰጥተውታል። አጤ ቴዎድሮስ ደፋር ልበ ሙሉ ጀግና ሴት ሆነ ወንድ ይወዳሉ። ትክ ብለው ሲመለከቱት ትክ ብሎ የሚያያቸው ሰው ይወዳሉ። አንገቱን የሚደፋ ወይም የማይከራከራቸው ዝም የሚላቸው ሰው አይወዱም ነበር።

በተፈጥሮአቸው አጤ ቴዎድሮስ አስከሬን ካዩ ከበቅሎ ወርደው አስከሬኑ ወደሚሄድበት ቤተ ክርስቲያን ሂደው አስከሬኑ ግብአተመሬት እስኪሆን ቆመው ይቆያሉ። ለቤተሰቦችም አጽናንተው ይሄዳሉ። ሌላው እርሳቸው ከሚያከብሩት ታላቁ ሙሽራ ሲሆን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሙሽራ ሲሄድ ሚዜው ብዙ ነው። ጥሩንባ እየተነፋ ጃሎ እየተባለ ይኬዳል።

ታዲያ በአንዱ ወቅት ዲያቆን ተድሮ ሚዜዎቹ ዲያቆናትና ወጣት ካህናት ስለሚሆኑ ከብዛታቸው የተነሣ ልብሳቸው ነጭ የጠመጠሙት ሻሻቸው ተራራ መስሎ ሲመጡ ያዩአቸውና አጤ ቴዎድሮስ እንደልማዳቸው ከበቅሎ ወርደው አለፉ አሉ። ሲመለከቱአቸው ንድድ አላቸውና "ሁላችሁ ቄሶችና ዲያቆናት ናችሁ ብለው ሲጠይቁ ሁሉም የሚመስገኑ መሰሏቸው አዎ ጃንሆይ" አሉ።

አጤ ቴዎድሮስ ቀበል አድርገው "መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ይከፈላል"ብለው ሲጠይቁ። እንኳን ከጠላ ጋር የዋለ የበስማም ቄስ በውሃ ቀንም ይህን ጥያቄ መመለስ አይችልምና መፋጠጥ ጀመረ። ለካ ሙሽራው ልበ ሙሉ ጎበዝ ተማሪ ኑሮ "እኔ ልመልስ ይፈቀድልኝ" ሲል ጠየቃቸው።



አጤ ቴዎድሮስም መልስ ሲሉት ጃንሆይ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት የሚከፈል ሲሆን እያንዳንዱ በምን እንደሚለይ አስረዳቸው። አጤ ቴዎድሮስ መልሱ ስላስደሰታቸው "ይህ ነው የአካልዬ ልጅ" ብለው ከዚህ በፊት ለማንም አድርገውት የማያውቁትን ለዚህ ዲያቆን ሙሽራ በቅሎአቸውን ሰጥተውታል።

አጤ ቴዎድሮስ አንዴ አልባሌ ልብስ ለብሰው ከወታደሮቻቸው መካከል ገብተው የሚሉትን ሁሉ ማዳመጥ ጀመሩ። ታዲያ አንድ ወታደር ምርር ብሎ ሲያማቸው ይሰሙና ወደ ድንኳናቸው ተመለሱ። ጥዋት አንድ አገልግል ባዶውን ሌላው አገልግል ብር ሞልቶ እንዲቀመጥ አደረጉ። የሁለቱም አገልግል አንድ አይነት ነው። ታዲያ ከሠራዊቱ መካከል ያንን ወታደር ወደ እሳቸው አስመጡትና እንዲህ አሉት። "ትናትና ምርር ብለህ ማማትህን አውቃለሁ።"

"አሁን ከፊትህ ሁለት አገልግል ተቀምጧል አንዱ ባዶ ነው፤ ሁለተኛው አገልግል ሙሉ ብር ይዞአል። ብር የያዘውን አገልግል ካነሳህ እግዚአብሔር ሰጥቶሃልና ትወስዳለህ። ባዶውን አገልግል ካነሳህ ግን በድልህ እዘን ስለዚህ ምረጥ" አሉት። ያ ወታደርም ቀሞ ሁለቱ አገልግሎች በጽሞና ከተመለከተ በኋላ "ይህን መርጫለሁ" ይላል። እርሳቸውም በሉ ክፈቱት ሲሉ አዘዙ። ነገር ግን ወታደሩ የመረጠው ባዶውን ነበር።

አጤ ቴዎድሮስ ሁለተኛውን አገልግል እንዲከፈት አደረጉ። "እኔ እግዚአብሔር በሚያውቀው ሰጥቼህ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አልፈቀደልህምና ሁለተኛ እንዳታማኝ" ብለው አሰናበቱት። የዚህን የአገልግል ታሪክ ብዙ ደራስያን ጽፈውታል።

# ምዕራፍ 11

## የባህል ልብስና የቁንጅና ውድድር ሥነ ጽሑፍ!

ተፈራ ኃይለ ሥላሴ፤ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 27 "ግማሽ አካል ብቻ የሚሸፍነውን የኢትዮጵያን የአለባበስ ባህል፤በእጇ ጠባብና በሱሪ እንዲተካ አድርገዋል" ሲሉ የእንግሊዝ ቆንስል ፕላውዲ ለአገራቸው መንግሥት የጻፉትን ደብዳቤ ጉዳይ ፈጻሚ (አምባሳደር) ተፈራ ኃይለ ሥላሴ ወደ አማርኛ ተርጉመው ጽፈውታል።

ከዚህ በፊት ስለ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ መጻሕፍትን ሳነብ "ግማሽ አካል ብቻ የሚሸፍነውን የኢትዮጵያን የአለባበስ ባህል በእጇ ጠባብና በሱሪ እንዲተካ አድርገዋል" የሚለውን ፈጽሞ አንብቤ አላውቅም።

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያውያን ከአለባበስ ጀምሮ ዛሬ በዓለም ላይ የሚያደንቀውን የተለያዩ የእስፖርት ውድድሮች ማድረጋቸው ተገልጧል። ከዚህ ላይ ሌላ አንድ አስቂኝ ተግባር ተፈጸመ። ያም አጤ ቴዎድሮስ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ጉድብ ለመሥራት በቁፋሮ ላይ ሳሉ አንድ ወታደር ያመልጠውና ሌሎች መሳቅ ጀመሩ።

አጤ ቴዎድሮስ ግን የሚወዱት ወታደር ስላመለጠው እንዳያፍር ብለው "እርሱ ጠንክሮ በመሥራት ላይ ሳለ ያመለጠው ከአቅሙ በላይ በመሥራቱ ስለሆነ ሽልማት ይገባዋል ብለው" ሸልመውታል።

አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 134 "በጎንደር ከተማ አቅራቢያ ቀሃ ወንዝ አጠገብ አጤ ሰቀላ ከተባለው ኮረብታ ላይ አጤ ቴዎድሮስ የቁንጅና ውድድር እንዲደረግ አዘዙ። የምርጫው ወይም የቁንጅና ውድድሩ ሊቃነ መናብርት ኢትዮጵያዊው ፊታውራሪ ገብርዬና እንግሊዛዊው ጆን (ዮሐንስ) ቤል ነበሩ። ራሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ባሉበት የቁንጅናው ውድድር ተካሄደ።"



"1ኛ ጣይቱ ይልማ ሆነች። ጣይቱ ይልማ ለውድድር የቀረበችው ከሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም ሲሆን የደጃዝማች ይልማ አስፋ ልጅ ናት።"

"2ኛ የወጣችው ወይዘሮ ተዋበች የተባለች ናት። ተዋበች እስላም ስትሆን ባልዋም መሐመድ ኩርማን ይባል ነበር። ተዋበች 2ኛ ለመውጣት የቻለችው በጠጉርዋ ማማር በቁንዳላዋ አወራረድና በሹርባዋ አረዛዘም ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፍ ገጽ 264 "የሴቶች ቁንጅና ውድድር እንዳደረጉ" ሲሉ ጽፈዋል። በኢትዮጵያ የሰውነት ማጠንከሪያ (እስፖርት)ከጥንት ጀምሮ ያለ ሲሆን ብዛት ያላቸውን የሰውነት ማጠንከሪያ ነገሥታቱ መመልከት ብቻ ሳይሆን ይጫወቱአቸው ነበር።

በተለይ የፈረስ ጉግስና ዋና ገበጣን መኳንንቱ ይጫወቱአቸው እንደነበር የታሪክ ሰነድ ምስክር ሲሆን ምክቶሽና ገና ጨዋታን፤ ንጥቂያንና ትግልን ሌሎችንም አዝናኝ ጨዋታዎች ታላላቅ ሰዎች እየተመለከቱ ወጣቶቹ ይጫወቱ ነበር። ዘመናዊው ደራስያን አጤ ልጅ ኢያሱን ከሚነቅፉበት አንዱ ፈረስ ግልቢያ ያዘወትራሉ እያሉ ነው። ሌሎችንም የሰውነት ማጠንከሪያ ዛሬ በአውሮፓ የሚደረገው ውድድር በኢትዮጵያ የነበረ ነው። በተለይ ነጻ ትግል የሚባለው ጨዋታ ዛሬ የአውሮፓ የሰውነት ማጠንከሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ብሀገሬ ላም ጠባቂው የሚጫወታቸው ጨዋታዎች ነበር።

ዛሬ በአሜሪካ (ቤዝ ቦል)ተብሎ የሚጠራው ግፊያ የሚበዛበት ጨዋታ ከኢትዮጵያ ዘሳን ላም ጠባቂዎች ተኮርጆ የመጣ ነው። ላም ጠባቂው ማታ ከብቱን ከበረቱ ካስገባ በኋላ ራቱን በልቶ ዳኛው በቡድን በቡድን ለይቶ ያሰልፋቸዋል። ከዚያም የጋለውን ደንጊያ በእርጥብ የእንጨት ልላጭ ይዞ ይወረውረዋል። ሁሉም የጋለው ደንጊያ ወደ ሄደበት እየሮጠ ይሄዳል። ደንጊያውን ያገኘው ሰው የሚፈልግ መስሎ ሩጦ ለዳኛው ያስረክባል።

ከነቁበት ግን ይይዙታል ሌላው ሲያነሣ አንዱ እጁን ሲበላ ሲጥለው ያኛው ሲቀበል ሲታገሉ አንዱ ቡድን አጥቅቶ ለዳኛው ያስረክባል ይህ ጨዋታ በሌሎች አገር የሌለ በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ነው። ይህ

አጤ ቴዎድሮስ በሥነ ቃል የበለጸጉ በመሆናቸው ለሥነ ጽሑፍም አስተዋጽኦ አድርገዋል። ቀን ተሌት የሚያደርጉትን ተከታትለው እንዲጽፉ ሰዎችን አዘጋጅተዋል ለዚህም ነው ዛሬ "እንጊ የጻፈው"እያልን ለምርምር የምንጠቀምበት ሥነ ጽሑፍ እንዲዳብር ስላደረጉ ነው። ትምህርት ቤት መከፈቱ የሥነ ጽሑፍ እድገት እንዲበለግጽ ጥረዋል።

በኢትዮጵያ ፊደላት በውጭ አገር የተጻፉትን መጻሕፍት ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ አስደርገዋል። ይህን ታሪክ በተከታታይ በሩሕ መጽሔት ከታሪካችን በተሰኘው ዓምድ ላይ ከፈለ ማሞ "የኅትመት ኢንዱስትሪ ታሪክ በኢትዮጵያ ከመርሐ ጥበብ ምሥረታ እስከ ውርሰ ዘመቻ"በሚል ደጋግመው ታሪክ ጠቅሰው ለንባብ አብቅተዋል። ረጅሙን ታሪክ ተወት አድርጌ ከአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሲደርሱ የጠቀሱትን አጠር በማድረግ ጥቅስ ልውሰድ።

ከፈለ ማሞ <u>ሩሕ መጽሔት</u> 1986 ዓም ገጽ 31 "በ19ኛው ምዕት ዓመት መግቢያ ላይ ሁለት ሌሎች ለኅትመት ኢንዱስትሪ መስፋፋት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ክስተቶች ነበሩ። ለሥልጣኔ አንጎሉ ክፍት የነበረውና ከዘመኑ ሰዎች በምዕተ ዓመት ቀድሞ አሳቢ የነበረው የቋራው ቴዎድሮስ ሊወለድ ሁለት ዓመት ሲቀረው ከ1818-1820 ባለው ጊዜ አባ አብርሃ በተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ የተተረጎመው የተሟላ መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ፊደላት በአማርኛ ቋንቋ ታተመ። ያስተረጎመው በካይሮ የፈረንሳይ ቆንስል ነበር።"

"ቆንስሉ ያንን ክቡር ትርጉም ለእንግሊዝ የባሕር ማዶ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሸጠው። የተባለው ድርጅት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እያተመ መሸጥን ቀጠለ። ሁለተኛ ሥልጣኔ አገራቸው እንዲገባ ሌት ተቀን አሳቢና ዓላሚ የነበሩት ቴዎድሮስ ለአገሩ መሪነት በበቁበት ዕድሜ በሚሲዮናውያን አማካይነት የመጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ መታተም ስለተረዱ በብዛት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና በመነኮሳትና በካህናት ሳይቀር እንዲነበብ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን አተጋጉ"።

"አጤ ቴዎድሮስ የገጠማቸው የሥልጣኔ እንቅፋት ለቁጥር የሚያታክትና እርሳቸውንም የሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ



ቢያደርጋቸውም በሕይወት እስካሉ ድረስ ያሳለሙት በዓይን ሒሲና ያልነደፉት ጅምር አልነበረም።"

"በተለይ ርእሰ ጉዳያችንን በሚመለከት በመቅደላ ላይ የከፈቱት የመጀመሪያ ቤተ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ውስጥ ኢንፎርሜሽን ወይንም እውቀት አብሮ ዜና የማከማቸት፣ የመጠቀም ለትውልድ የማስለታተፍና በአንድ ሥፍራ የማማከልን ተግባራት በበኩርነት የመሠረቱ መሪ ያደርጋቸዋል።"

"ከዚህም በቀር ንጉሠ ነገሥቱ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሌላቸው ሕዝቦች እንደባቢሎን ግንብ ሕዝቦች እየተናገሩ የማይግባቡ ሕዝቦች እንዳይሆኑ በማወቅ በዘመኑ ሲጻፍ የበቃውንና የሚጻፋበት ፊደላትም የነበሩትን አማርኛን የመንግሥት ሥራ ማካሄጃ የጋራ መግባቢያና የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ እንዲዳብር የሞከሩ ንጉሠ ነገሥት ናቸው።"

"አጤ ቴዎድሮስ አዋጅ አውጥተው አማርኛ የጽሑፍ ቋንቋ ይሁን ብለው ሳያስነግሩ ግዕዝን ተክቶ የሥራ ጽሑፍ ቋንቋ እንዲሆን ለማብቃት በማሰባቸው በጸሐፊ ትእዛዛቸው በደብተራ ዘነብ የተዘጋጀውን የራሳቸውን ታሪክ በአማርኛ እንዲጻፍ አደረጉ።"

"ቴዎድሮስ የአካባቢውን ግፊትና ተፅዕኖ በመቋቋም በውጭ አገር በኢትዮጵያ ፊደላትና ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም መንፈሳዊ መጻሕፍት ኢትዮጵያ እንዲገቡና እንዲነበቡ ያደረጉትኮ ለሕዝባቸው አንድ የሥልጣኔ ፍንጭ እንደሚያስገኝላቸው ስለተገነዘቡ ነበር። ይህንንም ግንዛቤያቸውን እ.ኤ.አ.በ1856 ዓም ማርቲን ፍላድ የተባለው ሚሲዮናዊ 300 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አምጥቶ ሲያስረክባቸው ከሰጡት መግለጫቸው እንረዳለን።"

"መጽሐፍ ቅዱስ የሰጡንና አሁን መንደሩ ባለመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሆን ሲሉ ደስታቸውንና ባለውለታነታቸውን ገልጸዋል። ስለዚህም ቴዎድሮስ በውጭ አገር በኢትዮጵያ ፊደላትና ቋንቋ የተዘጋጁ መጻሕፍት ወደአገራቸው እንዲገቡ የመግባቢያ የሥነ ጽሑፍና የመንግሥት ሥራ ማካሄጃ ቋንቋ እንዲደረጅ አርአያ በመሆን እውቀት ተወራራሽ ባህልና ሥነ ጥበባት በአንድ" ይቀጥላል ሲሉ ጽፈዋል።

ትግሬዋ የመቀሌ ተወላጅ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ልጃቸውን አጤ ገላውዴስን ለመርዳት የመጡትን ፖርቱጋሎች በማጠናከር ከፍተኛ ጀብድ የሠሩ ሲሆኑ በሌላው አንጻር የአጤ ግራኝ አህመድ ባለቤት እቴጌ ድል ወንበራ ጀግና ሴት ነበሩ።

በተለይም ራሱን ችሎ ስለ ሁለቱ እቴጌዎች ጥናት ቢደረግ በድርድር ወይም በፈረንጅ ቋንቋ በዲፕሎማሲ ተግባብተው ልጆቻቸውን እንዴት በእየጃቸው እንዳስገቡ ያስመሰግናቸዋል። ለምሳሌ አጤ አህመድ ግራኝ የማረኩትን ክርስቲያን ለዐረብ ባርያ ይሸጡ ስለነበር የአጤ ልብነ ድንግል ልጅ አቤቶ ሚናስ የኋላው አጤ ሚናስ፤ አቡዘቢብ ለባርነት ተሸጡ።

በአንጻሩ የአጤ ግራኝ አህመድ ልጅ ወገራ በአጤ ገላውዴዎስ እጅ ወደቁ። በዚህ ሰዓት ሁለቱ እቴጌዎች ተሳልከው ልጆቻቸውን ተመላልሰዋል። በጎንደር ከተማ ራሱን ችሎ የሚገበኝ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያንን ያሠሩት እቴጌ ምንትዋብ የንጉሠ ነገሥት አጤ በካፋ ባለቤት ሲሆኑ ባላቸው ሲሞቱ ከልጃቸው ከአጤ ኢያሱ ጋር ሁነው የኢትዮጵያን መንግሥት ሲመሩ ቆይተዋል።

ኋላም ልጃቸው አጤ ኢያሱ በካፋ ሲሞቱ ከልጃቸው ልጅ ከአጤ ኢዮአስ ጋር ሁነው የአገር መምራቱን ተግባር ተረክበው ሲያስተዳድሩ ኑረዋል። በዚህ ወቅት የአጤ ኢዮአስ እናት እቴጌ ቤርሳቤህ "ዛሬስ የአገር የማስተዳደሩ ተግባር ለእርስዎ ሳይሆን ለእኔ ይገባል ብለው" አማታቸውን ከሥራው አስወግደው እርሳቸው ከወሎ ኦሮሞዎች ቤተሰቦቻቸው ብዙ ጦር አስመጥተው መንግሥት መምራት ጀምረው ነበር።

ምንም እንኳን የዘመነ መሳፍንቱ አስተዳደር ይሁን እንጂ የትንሹ ራስ አሊ እናት እቴጌ መነን ጀግና መሆናቸውን የሚያሳየው ደጃዝማች ካሣን ለመግጠም ራሳቸው ጦር መርተው የሄዱ ናቸው። የልጃቸው ልጅ የአጤ ቴዎድሮስ ሚስት እቴጌ ተዋበች አሊም ለልጅ ካሣ አንድ የብልት ሥጋ አያታቸው እቴጌ መነን በመላካቸው በመበሳጨት ሲያንቃቁአቸው እንዲህ ብለው ነበር።

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 43 "የትግሉ ተካፋይ የሆነችውና የሚወዷት ሚስታቸው ወይዘሮ ተዋበች በሁኔታው ከርሳቸው ይልቅ አጥብቃ ስለተቆጣች ልክ ካሣ ወደተኛበት ክፍል ገብታ ከአጠገባቸው ቆም ብላ እንዲህ እያለች ታንቃቃቸው ጀመር። ሲሆን መጥኑ ተግበስብሶ በተቀበሉን ነበር? በቀርስ ድልብ ፍሪዳ ቀሚስ ለብሶ ሥጋው በመልክኛ ጠጁ በግንቦኛ በተላከልን ነበር? እንዴት እንደምን ብንናቅ ነው አንድ ብልት ሥጋ የተላከልን ከአለች በኋላ በተጨማሪ ጀግኖችን እወዳቸዋለሁ፥ አከብራቸውአለሁ ፥ፈሪዎችን ግን እንቃቸዋለሁ አብሬአቸው ለመኖርም አልፈቅድም፥ የሚል ኃይለ ቃል ታሰማ ጀመር" ሲሉ ጽፈዋል።



አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር አታካሮ ከገቡ በኋላ ቀሳውስቱ እርሳቸውን ለመጣል ያልተቆጠበ ጥረት አደረጉ። ከሥልጣን ለመጣል ብቻ ሳይሆን አጤውን ለመግደል ሞክረዋል። ካህናቱ አጤ ቴዎድሮስ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ሲቀርቡ መርዝ ጠቅቅለው ሊያቆርቧቸው ሲሉ ነቁባቸውና "በመጀመሪያ አንተ ቁረብና እኔን አቁርበኝ" ብለው ሲያፈጡበት ራሱ ቀምሶ ፍግም ብሏል።

አንድ ወዳጄ በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው "ስሜን አትጥቀስ ካህናቱ በሕይዎት እያለሁ ከኅብረተሰቡ ጋር እንድኖር አያደርጉኝም። ታሪኩን ግን እየተረጎምኩኝ እነግርሃለሁ" ሲሉ ቃል አስገብተውኛል። እኔም ትክክለኛ ስማቸውን አልገልጽም። እርሳቸው በዚህ ስም ተጠቀም ሲሉ በሰጡኝ ስም አሰግድ ድሌ እያልኩኝ እጽፋለሁ። እኔ የሰማሁትን ታሪክ ቁሶችን ፈርቼ ሳልጽፈው አልቀርም።

አቶ አሰግድ ድሌ <u>በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ</u> ያላቸው "አጤ ቴዎድሮስ ከካህናቱ ጋር እየተካረሩ ስለመጡ እነሱም አልተኙላቸውም። አጤው ከቦታ ቦታ ሲንከራተቱ ደብረታቦር ላይ ካህናቱ እቴጌ ተዋበች ሲቆርቡ መርዝ አቅምሰዋቸው በዚሁ ምክንያት ታመው ሞቱ" ሲሉ ነግረውኛል። አጤ ቴዎድሮስ የአገራቸው ፍቅር እያንገበገባቸው ባለበት ወቅት ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች አሊ ነሐሴ 13 ቀን 1850 ዓም ሞቱ። ከፍቅራቸው ብዛት የተነሣ አስከሬን ይዘው እስከ ጥቅምት 11 ቀን 1851 ዓም አልቀበሩአቸውም ነበር። ሬሳ ተሸክመው አገር ለአገር ሽፍታ ለማደን ይዞሩ ነበር። መቅበራቸው አልቀረምና ከቀበሩ በኋላ ይህን ሲሉ አንጎራጎሩ።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አባባል ከውጭ ውላችሁ ተርባችሁ ከቤት ለመድረስ እየሮጣችሁ ስትመጡ ከጓሮ ስትደርሱ ትዝ የሚላችሁ ጭቅጭቅ ከሆነ ራባችሁ ትቶአችሁ ይሄዳል:: አንጀታችሁ እጥፍ ብሎ ጭቅጭቅ ፈርታችሁ ጓሮ ለጓሮ ስትዞሩ ታመሻላችሁ:: እውን እንዳይሆን ሕልም ያድርግላችሁ:: ደግነቱ አሁን በምግብ ቤት በልቶ ለምኝታ ይመጣል:: ይህ ደግሞ ያለው በከተማው እንጂ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወንዶች ይህን እድል አያገኙትም::

አጤ ቴዎድሮስ የገጠማቸው ይህ ዓይነት ችግር ነበር:: እርሳቸው በእቴጌ ተዋበች የለመዱት ከቤት ሲገቡ ቀን የዋሉበትን ጭቅጭቅ የሚረሱበት ደስታ እንጂ ሌላ ጭቅጭቅ የለባቸውም ነበር:: እቴጌ ጥሩወርቅ ግን ካልተጨቃጨቁ ምግብ የማያቀርቡ ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት የሚወዱአቸው ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዓሊ ከሞቱ በኋላ እቴጌ ጥሩወርቅን ከአገቡ ወዲህ ነው:: እኒህ እቴጌ ጥሩወርቅ ጠባያቸው አስቸጋሪና አናዳጅ ሆኑባቸው:: እንኳን አሜሪካና አውሮፓ ኢትዮጵያ ያላችሁም ብትሆኑ ርእሰ ብሔር ክሊንተን ከወይዘሪት ሞኒካ ጋር መማገጣቸውን በተመለከተ በዓለም ጋዜጠኞችና ቀላጆች ተውኔት መጫወቻ ሁነው ነበር:: በዚህ ወቅት ወይዘሮ ሒላሪ ክሊንተን ስለ ባለቤታቸው ምንም ዓይነት ቅይምታ ሳያሳዩ ቀርተዋል:: በዚህ ምክንያት ርእሰ ብሔሩን የሚጠሉ ሰዎች ያሉ ቢሉም ከሥልጣናቸው ሳይወርዱ ቀናቸውን ጨርሰው ለቀዋል::

በዚህ ወቅት ባለቤታቸው ከሕዝብ መገናኛውና ከሪፓፐሊካኑ ጋር ቁመው ቢሆን ኑሮ ርእሰ ብሔሩ የቀራቸውን ዓመት አይጨርሱም ነበር:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ወይዘሮ ሒለሪ ወይም (ፈርስት ሌዲ) አስተዋይ በመሆናቸው ነው:: አንባብያን ልብ በሉ በተለይ ትዳር ያላችሁ ሁሉ ከሥራ ውላችሁ ከቤት ስትገቡ በትዳራችሁ ውስጥ ያለው መልካም ገጽታ ከሆነ እናንተም ቀን ተበሳጭታችሁ ብትውሉ እንኳን ከቤት ስትገቡ የሚጠብቃችሁ ጉምጉምታ የዓይን ግልምጫ ከሆነ እንቅልፍ ሳትተኙ ታድሩና ጧዋት ሥራ ስትገቡ ምን ዓይነት ስሜት እንዳላችሁ በራሳችሁ ታዘቡ:: ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የአበው ንግግር ልውሰዳችሁና "ከቤቱ በታች አቀበት ያለበት ሰውና ተጨቃጫቂ ሚስት ያለው ሰው አንድ ናቸው" ይላሉ::



## ምዕራፍ 2

## አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት!

"ይሉኛል ይልኛል ጨካኝ
ሀሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ"
ይሉ ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ በገና ሲደረድሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ከመጨከናቸው በፊት የምሕረት አዋጅ ያወጣሉ:: ከዚያም ምሕረት ማድረጋቸውን ያስነግራሉ:: የተናቀውንና የተጠላውን ሥራ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሁነው ይሠራሉ:: ዶማና መጥረቢያ ይዘው መንገድ ሲሠሩ ይውላሉ::

የወጣውን አዋጅ ቅድሚያ ራሳቸው ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ከዚያም ወታደሩና የመንግሥት ሠራተኛው ተግባራዊ እንዲያደርግ ያዛሉ:: ለምሳሌ ቁባቶቻቸውን ትተው ከእቴጌ ተዋበች ጋር በሥጋ ወደሙ እንደተወሰኑት ዓይነት ማንኛውንም ራሳቸው ቅድሚያ ያደርጋሉ:: ሌላው ቀርቶ መንገድ ሥራ ሳይቀር እርሳቸው ተሰልፈው ሠርተዋል::

<u>ኢትዮጵያና ዕድሏ</u> የተባለው መጽሐፍ ገጽ 120 "የብረታ ብረት ሥራ፤የእጅ ሙያ ሁሉ በኢትዮጵያ ልምድ እንደነውር ይቆጠር ስለነበር ቴዎድሮስ ያንን መጥፎ ልምድ ሰብረው እራሳቸው እንደ አንድ ወዛደር ዶማና መዶሻ ይዘው ሙሉ ቀን ከሕዝቡ ጋር በመቆፈርና በመቀጥቀጥ የመጀመሪያውን ዘመናዊ መንገድ በኢትዮጵያ ያሠሩ እሳቸው ናቸው::"

"ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የመንገድ ሥራ አልተለመደም ነበር በማለት አገር ጎብኚ የነበሩት አቶ ኤሚል ዮንቮ የተሰኙት ፈረንሳዊ ሲመሰክሩ የቴዎድሮስ እስረኛ የነበሩት ዶ/ር (አቶ) ሄንሪ ደግሞ ቴዎድሮስ ራሳቸው ከሕዝቡ ጋር ሆነው ጀንበር ወጥታ እስክትጠልቅ ድረስ ድንጋይ በመሸከም መሬት በመደልደል ይሠሩ ስለነበሩ ሕዝቡም ምግብና መጠጥ ሳያምረው ሙሉ ቀን ሲሠራ ይውል ነበር

"ተከሳሹ በዚህ ጊዜ አድራጎቱ የተወደደለት መስሎት አዎን እርግጥ ነው ብሎ መለሰ። አጤ ቴዎድሮስ አዎንታን በሰሙ ጊዜ በዚያ ሁሉ ሰው መሃል ካሣ የመይሳው ልጅ ብለው ፎከሩና አያችሁ በኔ ስም አራዊት ጅብ ሳይቀር ሲገዛና ሲዳኝ የሌት ሌባ ጅብናአውሬ ነው። ይሄው አውሬ በቴዎድሮስ አምላክ ሲባል ቀጥ ብሎ ቆመ፡ ብለው ለመኳንንቱ ሁሉ አሰሙ።"

"ቀጥለው ግን ተከሳሹን ተበረትህ ምን ያህል ከብት አለህ? አሉና ጠየቁት። እሱም ተጥጃውም ተምኑም ብዬ አምስት መቶ ያህል የቁም ከብት አለኝ አለ። ስንት ልጆች አሉህሳ? አሉት። ምሽቴ መካን ናትና ልጅ የለኝም ብሎ መለሰ። እንዲህ ተሆነ መልካም አንተ በቴዎድሮስ አምላክ ቁም ብትለው ታመለጠህ ወዲያ ተዳኝቶ እሱ ሌባው ቢቆምልህ አንተ ሳትዳኝ ወግተህ ጣልኸው፤እንዲህ ተሆነ እኔን የኔን ስም ነው እንጂ የወጋህ እሱን አይደለም፤ ስለዚህ ከሳሽህ እኔ ነኝና መኳንንቱ ይፍረዱን፤ፍርድ ቢሰጥህ ዳን፤ቢነሳህ ተቀጣ፤ ብለው ንጉሡ ራሳቸው ከሰሱት። መኳንንቱም ሊቃውንቱም አንድ ሆነው እንዲህ ብለው ፈረዱበት። በሩጫ ተፈታትነው በጉልበት ተሞካክረው አባራሪው ከተባራሪው ለመድረስ ሰንፎ ባይሆንለት ባምላኩ ብሎ ያመለጠውን ከሰሰ። እኔም ተከሰሰኝ ለሥርዓት እንጂ ለመወጋት አላስበኝም ብሎ ተዳኝቶ ቆመለት።"

"እሱ ከሳሹ ግን ሥርዓቱን ትቶ ወደ ጉልበቱ ተመልሶ ወጋውና ጣለው። ይሄን ታደረገ ቀኝና ግራ ተካሶ ቁሞ ተዳኛ ፊት ተሙግት መሃል አንዱን አንዱ መግደል ያለ ነውና አደባባይ ወጥቶ ተዛፍ ላይ ይሰቀል በቃ ብለው ፈረዱበት። አጤ ቴዎድሮስ ግን ብቅል ይመስል እሱን ተመሰቀል ይልቅ በሱ ንብረት ያ የተወጋው ይግባበት።"

"ወጊውም እስር ቤት ገብቶ በጅቦ (የእግር ብረት) ይታሰርና ዕድሜው ይፍታው። ምሽቱ ግን በሱ አበሳ አትወረስምና ጣማ ገንዘቧን (የደከመችበትን ገንዘብ) ተወራሹ ጋር ተካፍላ ትሂድ ብለው ፈረዱ" ሲሉ ጽፈዋል። በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ብዙ ፍርድ ተፈርዶአል። ሁሉንም ፍርድ ከዚህ ምዕራፍ ላይ ማስቀመጥ ባይቻልም ለወደፊቱ ሌላው ትውልድና ጸሐፊ ሁሉንም ሰብስብ አድርጎ ራሱን የቻለ መጽሐፍ እንደሚያወጣው ተስፋ አለኝ።



# ምዕራፍ 5

## የአጤ ቴዎድሮስ ደግነት

ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው ገጽ 13 "ደጃች ብሩም ተያዙ በግንቦት 19 ቀን ነፍጥ ሳይተኩስ ጦርም ሳይወረውር ደጃች ብሩም ድንጋይ ተሸክመው ወደቁ። ደጃዝማች ካሣም ደንጋው ይነሣለት አሉ። ደጃች ብሩን ሸማ አስነጥፈው አስቀመጡአቸው። ደጃዝማች ካሣ እንዲህ ብለው ጠየቋቸው፤ አሁን እኔን ይዘውኝ ቢሆን (ምድን) ምንድን ባደረጉኝ አሉአቸው። ደጃች ብሩም እንዲህ አሉ። እርስዎን ብይዝዎ ለማየት አላደርስዎም ነበር። (አስገድለዋል)አስገድልዎት ነበር እንጂ አሉ" ሲሉ ጽፈዋል። ይህን ታሪክ አቶ ገሪማ ታፈረም ጽፈውታል።

አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 50 "ደጃዝማች ካሣ ተማራኪውን ብሩ ጎሹን አሁን ድሉ የርስዎ ቢሆንና እኔን ቢማርኩኝ ምን ባደረጉኝ ነበር አሉዋቸው። ደጃዝማች ብሩ ሲመልሱ እርስዎን ብይዝ ኖሮ ለማየትም አላደርስዎም አስገድልዎት ነበር አሉ። ደጃዝማች ካሣም እንዴት አድርጎ ለጠላቴ አሳልፎ ይሰጠኛል ብለው እግዚአብሔርን አመሰገኑ" ሲሉ ጽፈዋል።

ከዚህ በላይ የተነበበው ጥቅስ በሁለቱም በኩል ያለው እውነታ ግልጽ ነው። ደጃዝማች ብሩ በትክክል ደጃዝማች ካሣን ቢማርኩ ኑሮ የሚያደርጉትን የሆዳቸውን ተናገሩ። ደጃዝማች ካሣ ደግሞ ይህን የመሰለ መልስ ሲሰሙ ሳይበሳጩ መቅረታቸው ደግነታቸውን የሚገልጽ ነው። ደብተራ ዘነብ ከጻፉት የሚያስረዳው ነገር ቢኖር አጤ ቴዎድሮስ ከጦርነት ላይ የማረኩአቸውን ሰዎች መልቀቃቸውን ነው። ከደብተራ ዘነብ አተራረክ ጋር የሚመስል ቆንስል ፕላውዴ ለአገሩ መንግሥት የጻፈው ደብዳቤ የደብተራን ዘገባ አጠናካሪ ነው።

የኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 26 "የተሸነፉ ጠላቶችን አካል ማጉደል ከልክለዋል። ሊጋስነታቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ወደር የሌለው ነው። ድል

የግብፅ ግዛት ናቸው ብሉ አወጀ፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም በወሰን ላይ ከኢትዮጵያ ጋር ብዙ ጦርነቶች ተደርገው ኢትዮጵያውያን እያሸነፉ የግብጽን ጦር መልሰዋል”፡፡

“የኦርቶዶክሱ ፓትርያርክ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በፈረንሳይ በኩል ለእማላጅነት ሲመረጡ ይህን የወሰን ጉዳይ በሰላም ለማስጨረስ መንገድ ለማዘጋጀት እንደሚሹ ለመሐመድ ሰይድ ፓሻ አመለከቱ፡፡ ሰይድ ፓሻም ለፈረንሳይ አማላጅነት አስመስለው ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም ጥያቄውን በደስታ ተቀብለው በታኅሣስ ወር 1849 ዓም ወደ ኢትዮጵያ መጡ፡፡ ምናልባት የማያውቁ አንባቢዎች ቢኖሩ በዚያ ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት ለኢትዮጵያ ጳጳስ የሚመጣላት ከግብጽ አገር ግብጻዊ የሆነ ሰው በፓትርያርኩ እየተሾመ ነበር፡፡ ስለዚህ የፓትርያርኩ የአቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ክበሬታ ነበራቸው፡፡”

“አቡነ ቄርሎስ እንደመጡ አጤ ቴዎድሮስና ሕዝቡ ታላቅ አቀባበል አደረጉላቸው፡፡ ከአቀባበሉም ሥነ ሥርዓት በኋላ አቡነ ቄርሎስ ከግብጽ ገዥ ከመሐመድ ሰይድ ፓሻ ለአጤ ቴዎድሮስ የተላከውን ደብዳቤ አቀረቡ፡፡ የመጡበትም ምክንያት በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የጠበቀ ወዳጅነት ለመመሥረት እንደሆነ በማስታወቃቸው ቴዎድሮስ በጣም ተደሰቱ፡፡ ይህንንም የሁለቱን አገር ወዳጅነት ቴዎድሮስ በጣም እንደሚፈልጉት ገልጸው ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ መልስ እንደሚጽፉ ገለጹላቸው፡፡ አቡነ ቄርሎስ ለሰይድ ፓሻ የሚላከውን የወዳጅነት ደብዳቤ ቀደም ብለን ታሪካቸውን ካነበብነው ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ጋራ ለማዘጋጀት ቢፈቀድላቸው ለማዘጋጀት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለቴዎድሮስ ገለጡ”፡፡

“አጤ ቴዎድሮስም ጉዳዩን በቅን ልቦና ተመልክተው በቴዎድሮስ ስም የሚላከውን ደብዳቤ እንዲያዘጋጁ ፈቀዱላቸው፡፡ በሁለቱ ጳጳሳት የተረቀቀው ደብዳቤ ለአጤ ቴዎድሮስ ቀረበ፡፡ አጤ ቴዎድሮስም የደብዳቤውን ረቂቅ ቃሉን ሰምተው ጉዳዩን በጉባኤ ለማስፈቀድ መኳንንቱንና ሕዝቡ እንዲሰበሰብ አዘዙ፡፡ መኳንንቱና ሕዝቡ በተሰበሰበበት ጉባኤ ለሰይድ ፓሻ የተጻፈው ደብዳቤ ተነበበ፡፡ ደብዳቤው ባጭሩ የሚለው ÷ጥበበኞች እንዲላኩላቸው በሦስት



የቱርክ መኮንኖች የሚመሩ የግብጽ ወታደሮች በኢትዮጵያ ያሉት የእንግሊዝና የጀርመን ዜጎችም እንዲወጡ የሚልና ወሰኑንም በሰላም በፓሻው አስተሳሰብ ለመጨረስ ፈቃደኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ነበር፡፡ ይህም አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ባዶዋን ሆና ከውስጥ የቱርክና የግብጽ ወታደሮች ገብተው ማንኛውንም የኃይል ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ የታሰበ ነበር፡፡”

“አጤ ቴዎድሮስ ደብዳቤውን ካስነበቡ በኋላ ፓትርያርኩ በቃል የነገሩአቸውን ጭምር ለተሰበሰበው ሕዝብ ነግረው የእግዚአብሔርን መንገድ ማስተማር ትታችሁ ለገዥያችሁ ለሰይድ ፓሻ አሽከር ከሆናችሁ እኔም በአገሬ ገዥያችሁ ነኝና በመንገዴ አስራችኋለሁ ብለው ፓትርያርኩንም ጳጳሱንም አብረው አሰሩአቸው፡፡ የዚያን ዘመን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የቤተ ክህነት ሰዎች በመሆናቸው ከአቡነ ቄርሎስና ከአቡነ ሰላማ መታሰር ላይ ሲደርሱ የታሰሩብት ምክንያት ብዙ ነው እያሉ ያልፉታል፡፡ አንዳንዶችም ቴዎድሮስ ስላበዱ ነው ይላሉ፡፡ ቴዎድሮስ ግን እንደዚያ የሚያደርጋቸው የአገር ፍቅር እንጂ እብደት አልነበረም” ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ሌላው አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ደግሞ የግብጾችን ሴራ አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፡፡

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 130 “ፓትርያርኩ መንፈሳዊ ልጆቼን እኅበኛለሁ ብለው ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ አባታዊ ጉብኝት ለማድረግ ቢነሡና ፈቃድም ሲሰጣቸው በግብፅ ለሚገኘው ለመንበረ ፓትርያርኩ የማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ገንዘብ ለማግኘት ነበር፡፡ ነገር ግን እውተኛ ተልእኳቸው ይህ ሳይሆን ቀይ ባሕርን አካለው ለያዙት ለቱርኮች ምልጃ ነበር የመጡት፡፡”

“ይህ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለእስላም አማላጅ ሆኖ መምጣት አጤ ቴዎድሮስን አናደደና ፓትርያርኩ ወደ እስር ቤት እንዲገቡ ተደረገ፡፡ የፓትርያርኩ እስራት በሰላማዊ ድርድር ቢቋጭም ለኢትዮጵያ የተመደቡት ጳጳስ ግን ሕዝቡ ለአጤ ቴዎድሮስ እንዳይገዛ ፓትርያርኩን አስረዋል በማለት መቀስቀሻ አደረጉበት፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን አድማ ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታ አርቆ ያሰበውን የቴዎድሮስን ራእይ እንዲቀጭ ዙሪያውን

አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ <u>የቋሚ ምስክርነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 79 "ጠላት ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ብዙ ችግር ፈጥሮባቸው ነበር፤ማለት 2ቱን ገደላቸው አንደኛውን አጋዛቸው:: አቡነ አብርሃም ብቻ እግዚአብሔር አድኗቸው በክብር እንዲገኙ ስላደረጋቸው ጣሊያን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆኑና ጳጳሳት እንዲሾሙ አድርጓል:: ስለዚህም ብዙ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሹመዋል:: እርሳቸው በክብር ሲያርፉ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ሁነው አሁንም እርሳቸው ብዙ ጳጳሳት ሹመው መሥራት ሲጀምሩ ጣሊያን ድል ሆነና" ሲሉ ጽፈዋል::

በ1933 ዓም ኢትዮጵያ ከወራሪ ነጻ ስትወጣ ኢትዮጵያውያን ግብጻውያንን ማየት አይፈልጉም ነበር:: በዚህ ምክንያት በተደረገው ድርድር ቀደም ሲል ተሹመው የመጡት ግብፃዊ አቡን እስኪሞቱ ድረስ መጠበቅ እንዳለብን ተስማሙ:: አቡነ ቄርሎስ በዕድሜ መግፋት ዐረፉ:: ከዚያም በኋላ ኢትዮጵያዊው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሁነው ተሾሙ:: እርሳቸው ሲያርፉ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሁነው ተሾሙ:: እርሳቸውን ጳጳሳቱ ከደርግ ጋር ተመሣጥረው እንዲታሰሩና እንዲገደሉ አደረጉ:: ከዚያም ገዳማዊው አባ መላኩ በደርግ መንግሥት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ተሾሙ::

እርሳቸው ሲያርፉ አቡነ መርቆሬዎስ ተሾሙ:: የደርግ መንግሥት ሲወድቅ ከደርግ ጋር አብሮ የሠራው ሁሉ እንዲወድቅ በመደረጉ ከቦታው እንዲነሡ ብዙ ውስብስብ ሴራ ተካሀዶ ከሥልጣናቸው ተነሡ:: እርሳቸው አዲስ አበባ እያሉ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሁነው ተሾሙ:: የሚገርመው ነገር ደግሞ እበላ ባይ ደራሲ መጽሐፍ ጽፈው "አቡነ መርቆሬዎስ መንጋቸውን በትነው ተሰደዱ" ይላሉ::

ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓም ሲሾሙ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አዲስ አበባ ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ነው በአቶ ክንፈ ገብረመድኅንና በአቶ አባይ ፀሐይ፤ውትወታ በጥር 1985 ዓም ትተው የተሰደዱ:: በሌሎች ፀሐፊዎችም ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስን ለማስደሰት ሲሉ ብዙ ተጽፏል፡ብዙም ተተርኳል፤በምስል ድምጽ በንባብ ተቀንባብሮ ዲቪዲ ተሰራጭቷል::



ጸሐፊ ተወልደ ገ/ጊዮርጊስ <u>ሰማዕት ዘእንበል ደም</u> የተባለ የምስል ድምጽ ክር በ2000 ዓም ውጥቷል:: ይህ የምስል ቅንብር የዲቪዲ ክር የሚያሳየው ታሪክ ቢኖር ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስን ለውርደት የሚዳርግ ነው:: ምክንያቱም ብዙ ስህተት አለበት:: ስህተቱ "ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በ1967 ዓም መጨረሻ ላይ ወደ ኢትዮጵ እንዲመጡ ጠሩአቸው:: አባ ገብረ መድኅንም የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርታቸውን አቋርጠው ጥሪውን ተቀብለው ወደ ኢትዮጵያ መጡ" ይላል:: ሌላም ሌላ ብዙ ስህተት አለበት:: ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስ ከ1967 ዓም በፊት አዲስ አበባ ገብተው ሥራ መያዛቸውን ደግሞ የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ያብራራል::

<u>ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ</u> ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 60 "በአባ ገብረ መድኅን ገብረ ዮሐንስ ሥራ ከፍተኛ እምነት የሚጥሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሉስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መጀመሪያ መስከረም 6 ቀን 1967 ዓም የኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ አድርገው ሲመድቧቸው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ ባሳዩት እንቅስቃሴና መረጋጋት አከታትለው የኮሚሽኑ ተ/ሥራ አስኪያጅ አድርገው በራሳቸው ፊርማ መድበው ሾመዋቸዋል" ይላል:: የሚጽፉት ከልባቸው ስላላይደል ለእበላ የተሰለፉ በመሆኑ ግድም አይሰጡትም::

• <u>የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ አጭር የሕይወት ታሪክ</u> የተባለች መጣጥፍ ገጽ 23 "በ1967 ዓም ቅዱስነታቸው ከአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ እውቅናቸውና አገልግሎታቸው የተነሣ ከሌሎች ሁለት አባቶች ጋር ለጵጵስና ተመርጠው በሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንብሮተ እድ ጵጵስና ተሹመዋል" ይላል::

እርሳቸው ጵጵስና የተሾሙት መስከረም 16 ቀን 1968 ዓም ሲሆን ደርግ ያስራቸው መስከረም 28 ቀን 1968 ዓም ነው:: ደራስያኑ ዝም ብለው ቅዱስ ቢያደርጓቸውም ታሪክና የባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ ደም እኮ በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አልደረቀም:: ይህ ብቻም አይደለም በ2001 ዓም ጳጳሳትን አስደብድበዋል:: ቤተ ክህነትን

"ደጃች ጎሹም እዚያው እየተወዳጃችሁ ነው እንጂ ቤቱ ተሠውሮ አይደለም ብሎ እሄዳለሁ ጫኑ አለ። መኳንንቱም ያዋርደናል አይሆንም ባይሆን ታማኝ ሰው ሄዶ ይያዘው አሉ። ደጃች ጎሹም አይሆንም ሰው አላምንም ብሎ ተነሣ።"

"አማሬ ኢየሱስ ከሚባል አገር ሲደርሱ አለቃ አርአያ ሰምቶ የእግረ መልስ ደገመ። ቀንደ መለከቱና ነጋሪቱ እንዳይጮህ ድምፅ የሚዘጋ አስማት ደገመ። የዚህ ጊዜ የነጋሪቱና የመለከቱ ድምፅ ሲዘጋ ሠራዊቱ ደነገጠ። አይሆንም እንመለስ ሌላ ቀን በድንገት አዘናግተን ሌሊት እንይዘዋለን ብሎ መኳንንቱ ደጃች ጎሹን ተቆጡ። ከዚያ ወዲህ ባትከና ወደ በኸራ ተመለሰ። በሌላ ቀን አዘንግቶ ድንገት በሌሊት አስይዞ ገርፎ ዋሚት ዋሻ አሠረው" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ደብተራ ሊጠሉበት የቻሉት ከላይ የተጠቀሰውን አለቃ አርአያን ለመያዝ ከሄዱት ወታደሮች አንዱ ሳይሆኑ እንዳልቀሩ አንዳንዶች ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም አጤ ቴዎድሮስ ደብተራን የጠሉት። ኋላም ከነገሡ ወዲህ ደብተራ ፈጽሞ አይወዱም ነበር። ከቄስ የበለጠ ግብር እንዲከፍል ያደርጉት ነበር። በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ደብተሮች አጤ ቴዎድሮስን የጠሉአቸው። የመምህር አካለ ወልድን የሕይዎት ታሪክ የጻፈው ደራሲ የደብተራውን ስም ጠቅሰው አብራርተዋል።

የመምህር አካለ ወልድ <u>የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 31 "አጤ ቴዎድሮስ ጭከናቸው ይነገራል እንጂ ዕውቀታቸውና ፍርዳቸው እጅግ አይነገርም። ነገር ግን ወልደ ሚካኤል የሚባል ደብተራ በተንኮሉ አእምሮአቸውን ሳይለውጠውና ሳያጠፋው እጅግ የሚያስደንቅ ፍርድ ይፈርዱ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ ደብተራ ሁሉ የአጤ ቴዎድሮስ ዓላማ እንዳይሳካ ያደረጉ ተንኮለኞች ናቸው። አይሠሩ አያሠሩ አንዱን ካንዱ ሲያጣሉ የሚውሉ ነበሩ። እነዚህ ደብተሮች ለአጤ ቴዎድሮስ ዓላማ አለመሳካት ዋናዎቹ ተንኮለኞች ሕዝቡ ከእርሳቸው እንዲርቅ ያደረጉ ናቸው። ዛሬም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ይቅርና አንዳንድ በስደቱ ዓለም የሚያመሳቅሉ መኖራቸው አይዘነጋም።



# ምዕራፍ 5

## አጤ ቴዎድሮስና መነኮሳትና ካህናት

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር <u>ምንኩስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናትና</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 91 "የሐሳውያኑን መነኮሳት ተንኮል የተረዱት አጤ ቴዎድሮስ ብቻ ነበሩ!የእነዚህ ሐሳውያን መነኮሳት ባሕታውያን ሰለባ ከሆኑት መካከል አጤ ዮሐንስ ይገኙበታል። አጤ ዮሐንስ ወደ መተማ ዘምተው እንዲሞቱ ምክንያት የሆኑት በአጤ ምኒልክ የተላኩ የቀበሮ ባሕታውያን ነበሩ" ሲሉ ጽፈዋል።

ካህኑ የጌታን ሥጋና ደም አስመልክቶ በቅዳሴ ጊዜ እንዲህ ይላሉ" ንጹሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበል! ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል! ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል! በልቡናው ቂምን የያዘ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ! እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ! እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ ደፍራችሁ ወደ ክርሥቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም። ኀጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ በንጽሕና ሁናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ" ብለው መነኮሳቱ ይናገራሉ።

ቃሉ መባልም ያለበት መሆኑን ከእኛ ይልቅ መነኮሳቱ ያውቃሉ ነገር ግን "ቂምን የያዘ" የሚለውን ቃል ራሳቸው ተናግረው ምዕመናኑን "አሜን" አስብለው ቂም በዝቶ የሚታይባቸው በመነኮሳቱ መሆኑ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ቀኛችሁን ሲመቱአችሁ ግራችሁን"ስጡአቸው አለ እንጂ ቂም ይዛችሁ ኑሩ ብሎ አላስተማረም። መነኮሳት ቃሉን ለምእመናን ያስተምራሉ።

አጤ ቴዎድሮስ መነኩሴ አይወዱም ነበር። ምክንያታቸው ሰነፍ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባረከውን ጋብቻ ሽረዋል ብለው ይነቅፏቸው ነበር። ከቄስና ከመነኩሴ ቄስን ይመርጣሉ። በነገራችን ላይ መነኩሴ ሁሉም አንድ ናቸው ማለት አይደለም ብዙ ጥሩ መነኮሳት ቀደሞም ነበሩ ዛሬም ደግሞ አሉ።

ሸህ ሁሴንና አጤ ቴዎድሮስ የተወለዱበት ዘመን አንድ ነው:: ምናልባት ወሩንና ቀኑን እንጂ ዓመቱ አንድ በመሆኑ አብረው የሡሩ ናቸው:: ሸህ ሁሴን የማይወዱት አጤ ዮሐንስን ሲሆን ቄሱ አጤ ሳያስተምሩ እስላሙን በማጥመቃቸው ምክንያት ሸህ ሁሴን ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 34

"ደረሱብን እንጂ መች ደረሰንባቸው
ቀረቡ ይሉናል የነፍስ አባታቸው" ሲሉ ተናግረዋል::

ሸህ ሁሴን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመምህር አካለወልድ ጋር በጣም ይግባቡ ነበር:: ሁለቱም ምሁራን በየጸሎት ቤታቸው ቆይተው ይገናኙና ብዙ ያወሩ ነበር:: ይህን ታሪክ በልጅነቴ አባ የሱፍ የምንላቸው ሸማኔ ከጓሯችን ሸማቃ ዘርግተው ይሡሩ ነበር:: በተለይ ከብዙ ፈተና በኋላ በ1973 ዓም ወደ ትውልድ መንደሬ ስመለስ ከእርሳቸው ጋር ቁጭ ብለን ስንጫወት እንውል ነበር::

ዛሬ ራሱን ችሉ መጽሐፍ የተጻፈላቸውን የሸህ ዘካርያስ የኋላውን የአለቃ ዘካርያስን ታሪክ አንድ ባንድ ዘርዝረው ነግረውኛል:: ታዲያ አባ የሱፍ ከአባታቸው የሰሙትን የሸህ ሁሴን ጅብሪልንና የመምህር አካለወልድን ታሪክ እንዲህ ሲሉ አጫውተውኝ ነበር::

<u>አባ የሱፍ</u> "ሁለቱ ከጸሎት ቤታቸው ከቆዩ በኋላ ሁሌም ይገናኛሉ:: ታዲያ አብረው ሲሄዱ የእስላም ሸህና የክርስቲያን መምህር አይመስሉም ነበር:: በዚህ ወቅት ደብተሮች ቀኑና ሊያጣሏቸው ፈለጉ:: ያልተባለ ነገር እየነገሩ ቢደክሙም መግቢያ ቀዳዳ አጡ:: በመጨረሻ ሊጣሉበት የሚችሉት በሃይማኖታቸው ስንመጣባቸው ነው ብለው አንድ ቀን ሁለቱ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር ቆይተው ሲወጡ አለቃ ፈንታ የተባሉት በኋላ በአጤ ቴዎድሮስ የተገደሉት እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው ሼህ ሁሴንን ፥ሸሁ ክርስቲያን ነው እስላም የሚጸድቅ፥በማለት ጠየቋቸው:: የአለቃ ፈንታ ቤረኝነት ሼህ ሁሴን እስላም ነው የሚጸድቀው ሲሉ መምህር አካለወልድ ደግሞ ክርስቲያን ነው ይላሉና ይጣላሉ ብለው አስበ ነበርና ይህን ጥያቄ ያነሡት:: ነገር ግን ሼህ ሁሴን ጅብሪል ይህን ሲሉ መለሱላቸው::"

"ከሁለቱ አንዱ ይገባል ገሐነብ
በተለይ ደብተራ ይሆናል የሚንገበገብ



ብለው አሳፈሩአቸው::"

"ልክ ዛሬ ተቆጥቶ መጥቶ ሰድቦኝ እንደሚሄደው ደብተራ ፈቃዴ የአክስትህ ልጅ ባል ዓይነት ደብተራ ነበሩ:: አለቃ ፈንታ አጤ ቴዎድሮስ ደብታቦር መድኃኔዓለምን አሡርተው አለቃ ይህ ቤተ ክርስቲያን ይበቃ ይመስልሃል ሲሉአቸው አለቃ ፈንታ ጃንሆይ መቾም ለሁለት ቄስና ለሦስት ሰሞነኛ ይበቃል አሉአቸው:: ኋላም እንዲሁ አጤ ቴዎድሮስ ወዳጅ መስለዋቸው አንድ ቀን አለቃ ይህ ካህናትና ደብተራ ሁሉ ጠገበኮ ቢሉአቸው አለቃ ፈንታ ጃንሆይ ጠግቦ መሬት ለቆ በማለት ተናግረው የተገደሉ ናቸው::"

ደብተራ ሲባል ነገረኛ ነው:: ልክ አለቃ ፈንታ ሼህ ሁሴንንና መምህር አካለወልድን ለማጣላት ጥሮ በሸሁ መልስ አፍሮ ተመልሶ ነበር ኋላ ግን ተቅለብልቦ አጤ ቴዎድሮስን በመጋፋቱ ተደብድቦ ተገሏል" በማለት ሡፋ አድርገው ታሪክ ጠቅሰው ለልጃቸው ለወንድማገኘና ለእኔ ይነግሩን ነበር:: መምህር አካለወልድና ሸህ ሁሴን ጅብሪል የኢትዮጵያ አንድነት መደፈር የሚያንገበግባቸው ምሁራን ነበሩ:: ለዚህም ሁለቱ አንድ ከብት አርደው ሥጋውን ተካፍለው በልተዋል:: ለዚህ መሠረቱ ደግሞ ለአገር አንድነትንና ለሃይማኖት ነፃነት ሁለቱም የሃይማኖት አባቶች ከአጤው ጋር ተስማምተው መሥራታቸው ዋና ምልክት ይመስለኛል::

<u>የመምህር አካለ ወልድ የሕይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 33 "አጤ ቴዎድሮስ ለእስላምና ለክርስቲያን አንድ በሬ ሲሰጡ ማን ያረደውን ማን ተካፍሎ ለመብላት ችግር ተፈጠረ:: ግን መምህር አካለ ወልድ እስላሙ ይረደው አሉና ታርዶ እኩል የተከፈለውን ሥጋ በስመአብ ብለው በመስቀል ባርከው በካራ እንደ መቁረጥ አድርገው ለካህናቱ ሰጥተዋል" ተብሎ ተጽፏል::

መምህር አካለ ወልድና ሸህ ሁሴን ጅብሪል አብረው ለኢትዮጵያ አንድነት ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር የታገሉ አባቶቻችን ነበሩ:: የመምህር አካለ ወልድ ታሪክ አልደበዘዘም በስማቸው ትምህርት ቤት ተሡርቷል:: ነገር ግን እየደበዘዘ የመጣ የሸህ ሁሴን ጅብሪል ተግባር ነው:: ለኢትዮጵያ አንድነት ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር አብረው የታገሉ መሆናቸው በሰፊው አልተብራራም:: እኒህ እንቁ የኢትዮጵያ ልጅ ተግባራቸው እንዳይጠፉ በስማቸው አንድ ተቋም ሊመሠረትላቸው

ይህ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቶያን ሥርዓት ሳይሆን የፕሮቴስታንት ሥርዓት ነው:: ሣታውቁት የፕሮቴስታንትን አሠራር በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያስገባችሁ ነው:: ዛሬ እሁድ ቁሞ ያስተማረውን ስብከት በክር አዘጋጅቶ ለገቢያ ማቅረብ ዋናው ትልቁ ገቢ ሁኖአል:: ለምሳሌ አባ ወልደ ትንሣኤ እያልነህ የሚያስተምሩት ትምህርት ተራብቶ ለምእመናን የሚያቀርቡት ቤተ ክርስቲያን እንጂ በእርሳቸው አማካኝነት አይደለም::

የእርሳቸው ፍላጎት ትምህርቱ ለምእመናን መድረሱ ብቻ ነው:: ይህ ነው የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንጂ ምጣኔ ሀብት ለመሰብሰብ በግል መስገብገብ ትክክል አይደለም ጥንቃቄ ይደረግበት:: ለካ የዚህ ዓይነት ካህናት በዝቶ ነው አጤ ቴዎድሮስን ሲያበሳጫቸው የነበረው::
አጤ ቴዎድሮስ አገራቸውን ለማሠልጠን ከፍተኛ የሆነ ፍቅር ኑሮአቸው ሲነሡ ግንባር ቀደም ወሬኞች የበስማም ቄሶች ካህናት ነበሩ ለእርሳቸው ጠላት የሆኑት:: ለዚህም ነበር አጤ ቴዎድሮስ "ታግዬ ያልጣልኩት የቄስን ጠብ ነው" ያሉት በልጅነታቸው የቄስ ትምህርት የተማሩ ከመሆናቸው በላይ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ስማቸው ያልተጠቀሰው መነኩሴ ጥሩ አድርገው አስተማሩአቸው::

እርሳቸውም የቄሱ ተንኮል አልጠፋቸውም ሁኖም ካሸነፋቸው መካከል ካህናት መሆኑ ራሳቸው ተናግረዋል:: የካህናቱ አድማ ግቡን የሚመታው ለምንድነው? በዛን ሰዓት ይቅርና ዛሬ ድረስ ካህናቱ የጠሉትን የሚያስጠሉበት ዘዴ ብዙ ነው:: የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ሳነብና ዛሬ የማያቸውን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተግባር ሳጤን እውነትም ቄስን ታግሎ መጣል አይቻልም:: ምክንያቱም ቄሶች የሚናገሩት ሁሉ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አለው::

ቄሶች አጥፍተው ሌላውን አጥፊ አድርገው ያቀርባሉ:: ከዚህ በፊት በጻፍኩት መጽሐፍ "የበስማም ቄሶች"እልክ ብለው የተወሰኑ ምእመናን ወቀሱኝ ለነገሩ አልረዳቸው ብለው እንጂ እንደ ካህን አድመኛና ሴረኛ የለም:: የቤተ ክርስቲያን ምእመን ሳያጠፋ አጥፊ ተብሎ ልጅ ቢወልድ ክርስትና አይነሣለት ስርግ ቢያደርግ አይባረክለት ለምን ተብለው ሲጠየቁ ከማስረዳት ይልቅ በደፈናው አጥፍቷል ብለው በሩን ይዘጋሉ:: እነሱ የወደዱትን ባላቸው ሥልጣን ተጠቅመው ለማስታረቅ ጥረት ሲያደርጉ እነሱ የተጣሉ እንደሆን



ታረቁ ሲባሉ ፈጽሞ ይላሉ ምእመናኑን በቀላሉ አሳምነው እነሱ የጠሉትን ግለሰብ ከኅብረተሰቡ አግልለው ያስጠሉታል::

አቶ ሀብተ እንደነገሩኝ "ቤተ ክርስቲያን አባል ሁኜ ሳለ የገንዘብ አቅም አንሶኝ መክፈሌን ካህኑ ያውቃሉ:: እሁድ እሁድ ሥለምስራ ቤተ ክርስቲያን አልሄድም:: ይህን ካህኑ አሳምረው ያውቃሉ:: ታዲያ አንዴ ስብሰባ ላይ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ላይ ውይይት ነበርና እኔ ስናገር ካህኑ ቅድሚያ እሁድ እሁድ ቤተ ክርስቲያን መሄድና አሥራት በኩራት የማይከፍል ሰው አስተያየት መስጠት አይችልም በማለት አሳፈሩኝ በማለት ነግረውኛል:: የዚህን ዓይነት ካህን ነበር አጤ ቴዎድሮስ "ሰነፍ እረኞች ስለሆናችሁ እግዚአብሔር ይፈርድባችኋል" ይሏቸው ነበር:: ታዲያ ለእንዲህ ያለ ካህን ሐጢያት ብሎ ቢነግሩት ፀሐይ ሳትገባ አገሩን የስማሁት ብሎ ያዳርሰው የለም እንዴ?

ት/ተ ሕዝቅኤል ም÷34÷3 "እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ የወፈሩትን ታርዳላችሁ በጎቹን ግን አታሰማሩም:: የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው:: እረኛንም በማጣት ተበተኑ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ::" ይላል::

የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ምእመናን ዛሬ ጠባቂ በማጣታቸው እየባዘኑ ናቸው:: በተለይ በዚህ በስደቱ ዓለም የቤተ ክርስቲያን ልጆች እየባዘኑ ናቸው:: ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን የሚያይበት መነጩር እንዳለው ከእኛ ይልቅ እነሱ ያውቃሉ:: በዚህ በአሜሪካን አገር አንዳንድ ካህናት ከሰበካ ጉባኤው ከቦርድ ጋር ይመረጡና አብረው ይሠራሉ::

ታዲያ ካህኑ በስብሰባ ከሰበካ ጉባኤው ጋር አልግባባ ሲሉ አስቀድመው" እንዳትናገር አውግዝሃለሁ" እያሉ አንዱን ሁሌ ያበሳጩታል:: በአንድ የሃሳብ ፍጭት ላይ ሊናገር እጁን ሲያወጣ ቄሱ የተለመደውን ውግዘታቸውን ሲጥሉበት "እኔም በመሃይም መብቴ አውግዤዎታለሁ እንዳይናገሩ" ብሉአቸዋል:: ይህን ያህል ነው ምእመናን በስቃይ ላይ ያሉት::

ሃይማኖታዊና ብሔራዊ መሪ ነበሩ። በዘመናቸው በኢትዮጵያ የነበሩትን ሚሲዮናውያን ሁሉ ሰብስበው ኢትዮጵያ የራሷ የወንጌል መምህራን አሏት። ይልቁንስ እናንተ የሠለጠናችሁበትን ለእኛም የሚያስፈልገንን ብረት ማቅለጥና መቀጥቀጥ ቴክኖሎጂ አስተምሩን ብለዋቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አጤ ቴዎድሮስ ብሔራዊ መሪ መሆናቸውን ተረድተው ትውልዱ እንዳይረሳቸው ጽፈዋል። ሰንፍ ካህናት ዛሬም ድረስ የሚጠላቸው መኖሩ አይዘነጋም። ነገር ግን ከጳጳስ እስከ መነኩሴ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲስፋፋ የሚፈልጉ ሁሉ ዛሬም ያከብሩአቸዋል። የሚያከብሩአቸው ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዳትጎሳቆል የሚያስቡት ብቻ ናቸው። ሆድ አምላኪዎች ካህናትማ ስማቸው እንዲጠራ የማይፈልጉ አሉ።

አባ ገሪማ (ዶ/ር) <u>የኢትዮጵያ ኦርቶቅዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር</u> በየዘመናቱ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 49 "የተወሰኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው አጤ ቴዎድሮስን ሊያወናብዷቸው ቢሞክሩም አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ ሃይማኖታዊና ሀገርን ወዳድ ኢትዮጵያዊ መሪ ስለነበሩ በወንበዴዎች ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ጽፈዋል።

እንዲያውም ብፁዕ አቡነ ገሪማ "በወንበዴዎች ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ካህናት ወንበዴዎች መሆናቸውን ተረድተዋል። በነገራችን ላይ ብፁዕ አቡነ ገሪማ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ላይ ወንበዴዎች መኖራቸውን የመሰከሩ መሰለኝ። ቤተ ክርስቲያን እንዳታድግ የሚያደርጉ ጳጳሳት መኖራቸውን በካህናት አስመስለው መግለጻቸው ነው። ይህ ተግባራቸው ዛሬም እየታየ መሆኑን ከመሰከሩ ለወደፊቱ እባክዎ እውነትን ብቻ ይዘው ውሸትን ትተው እንዲሰብኩ ይሁኑ።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓም</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 335 "የተወሰኑ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተገን አድርገው አጤ ቴዎድሮስን ሊያወናብዷቸው ቢሞክሩም አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ከተዋሕዶ ሃይማኖት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ነጥለው የማያዩ



ሃይማኖታዊና ሀገርን ወዳድ ኢትዮጵያዊ መሪ ስለነበሩ በወንበዴዎቹ ሙከራ ሊበረግጉ አልቻሉም" ሲሉ ጽፈዋል። ለዚህም ነው ዛሬ ድረስ አገራቸውን የሚወዱ ካህናት አጤ ቴዎድሮስን የሚወዱአቸው።

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 267 "ከካህናቱ መካከል በጥቅማቸውና በክብራቸው መነካት የተነሣ ግማሾቹ ሲጣሉዋቸው ብዙዎቹ ደግሞ በዘመነ መሳፍንት የነበረውን የእርስ በእርስ ጦርነት የየአውራጃውን መከፋፈል በጎንደርና በደብረታቦር ከተማዎች የነበረውን ድሎትና ቅንጦት መበርከት በመመልከት ጠንከር ያለ ሁሉን ተቆጣጥሮ የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ የማዕከላዊ መንግሥት መሪ በመጥፋቱ ይናደዱ የነበሩት የሊቃውንት ወገኖች በትንቢት የተነሡት ቴዎድሮስ የሚያደርጉትን ጥረት ከዘመናዊ ግንባታቸው ጋር በማያያዝ የሚገባ አድርገው ድጋፋቸውን እየሰጡ በወረብና በቅኔ የሚያበረታቷቸው ነበሩ።

ከነዚህም መካከል ቴዎድሮስ ራሳቸው ይማሩዋል እንደ አካልዬ ይዋጉዋል እንደ ገብርዬ ብለው ትምህርታቸውን ያደነቋቸው መምህር አካለ ወልድ ይገኛሉ። እርሳቸውም ቴዎድሮስ የመግደል የማዳን ሥልጣን ከአምላክ እንደ ተሰጣቸው ለርሳቸው አልገዛም ያሉት የሞት (ኩነኔ)እንዳገኛቸው የተገዙላቸውን ግን መንግሥተ ሰማያትን እንደ ወረሱ ለማመልከት ሥላሴ ቅኔ ተቀኝተውላቸዋል።

"እንደዚሁም በደረስጌ ከእቴጌ ተዋበች ጋር ስለ መንገሣቸው የተነገረው ቅኔ።"
ተዋቡን ሲያገባ ሠርጉ መች ደመቀ፤
ደረስጌ ስናየው መልሱ አንጸባረቀ፤
ፊትማ ሲያገባት ተከሊል መች ነበረው፤
ካሣ ደረስጌ ነው በሕግ የተዳረው፤
ሊቃውንት ካህናት ካንድ ላይ በሙሉ፤
ጎንደር አልነገሠም ብለው ያድማሉ፤
በከንቱ ነው እንጂ በራስ ፍርድ ለማምጣት፤
ዘውዱ ከተሰራ ሆኗል ዐስር ዓመት፤
ለኢትዮጵያ ሲበጅ ካየነው፤
የንገሡበቱ ደረስጌም ጎንደር ነው"

ዛሬማ ሩቅ ሳንሄድ ቁጥራቸው ትንሽ ተግባራቸው ትልቅ የሆኑት ኢትዮጵያውያን በችካጎ የተጀመረው በሲያትል መደገሙ በሌሎችም ኢትዮጵያውያን ባሉበት ቦታ ሁሉ ጠበሉ እንዲደርሳቸው በር ከፋች ሁኗል:: ከዚህ አገር ለመኖር በማኅበር መደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ወይዘሮ ሙሉእመቤት ረታ፤የሲያትል ማኅበር ሊቀ መንበር አስምረውበታል::

ወይዘሮ ሙሉመቤት ረታ አውራምባ ታይም ጋዜጣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 3 ጥር 2011 ገጽ" እንድነታችን በዚህ አገር ፖለቲካ ትልቅ አቅም አለው:: ሴናተሩም ሆነ ሌሎች ፖለቲከኞች የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ሲባል ሁሉም መምጣት ይፈልጋል:: ምክንያቱም ለእነሱ ይህ ድምፅ ነው:: ስለዚህ ችግሮቻችን ለማቅለል በኮሚኒቲ አንድ ሆነን መንቀሳቀስ አለብን::"

"የቱንም ያህል በፖለቲካ ልንለያይ እንችላለን እንደ ኮሚኒቲ ግን ውጤታማ የሚያደርገን ይህንን ኮሚኒቲ ስናጠናክረው እና ድምፃችን መሰማት ሲችል ነው:: ሕዝቡ ለዚህ ሕንጻ መግዛት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል:: አሁንም ይህንን ሁሉ ስኬት አብቅተን ወደ ኋላ እንዳንመለስ ሕዝቡ ሥራዬ ብሎ ኮሚኒቲውን እንዲንከባከብ አደራ እላለሁ" ሲሉ ተናገሩ::

ይህን የሲያትልን ሕንጻ እንዲገዛ ጥረት ያደረጉት ትንሽ ናቸው:: እነዚህ ኢትዮጵያውያን የማይሞት ልጅ በመውለዳቸው በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ:: "ሰው ሰው በመሆኑ ያልፋል:: ጥሩ ተግባር ግን ከመቃብር በላይ ይኖራል:: ስለዚህ በሌሎች በሉስ አንጀለስና በዋሽንግተን ዲሲና በአትላንታ ከተማ ያሉ ኢትዮጵያውያን ምን ይጠብቃሉ?

## ምዕራፍ 2

## በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የተሾሙ ሹማምት

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ በየደረሱበት ክፍለ ሀገር ባላባቱን ሹመዋል:: እንኳን በክፍለ ሀገር ደረጃ ቀርቶ በምክትል ወረዳ በየአካባቢው ታማኝ የሆነዉን ሹመውለታል:: በጎጃም ራስ እንግዳ የሁሉም ጠቅላይ ገዥ ሁነው በውስጣቸው ብዛት ያላቸው ባለ



ማዕረጎች ሹመዋል:: ትግሬንም ለራስ ባርያው እና ለራስ ኃይለ ማርያም ሲሾሙላቸው ባሕረ ነጋሽን በውስጣቸው አድርገው እንዲቆጣጠሩ አድርገዋል::

የባሕረ ነጋሽ ተወላጆች በራስ ባርያው አቅራቢነት ተሹመዋል:: በተለይም የካቶሊክን ካህናትና የፈረንሳይን ወኪሎች ለመያዝና ለመውጋት የተዘጋጁትን የሐማሴን ተወላጆች በራስ ባርያው አቅራቢነት ከአጤ ቴዎድሮስ ፊት ቀርበው ሹመት የጸደቀላቸው ባላባቶች ናቸው:: ወሎን ድል ካደረጉ በኋላ ሰቆጣን ለደጃዝማች ገብረ መድኅን ማለትም ለአጤ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ሌሎችንም አውራጃዎች እንዲሁ ባላባቱን ሹመውበታል:: ሸዋን እንደተቆጣጠሩ ለባላባቱ የኅህለ ሥላሴን ልጅ መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤልን በሸዋ ሾሙ::

ታሪክ አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 111 " መርድ አዝማች ኃይለ ሚካኤልን በሸዋ ሾመ:: ለአቶ አንዳርጋቸው አበጋዝነትን ሰጥቶ በየአለበት ጸና:: የኅህለ ሥላሴ ሥርዓት ይርጋ ብሎ አዋጅ ነገረ" ሲሉ ጽፈዋል::

በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በሃይማኖትም በኩል ቢሆን መሪዎች ነበሩ:: በተለይ በክርስቲያኑ መምህር አካለወልድ፤በእስልምናው ሼህ ሁሴን፤በአራቱ ሃይማኖት ካህን ሙሴ የተባሉ መኖራቸውን የሚናገሩ አሉ:: በተለይም በግእዝ የተጻፈ መጽሐፍ ያላቸው አቶ አሰግድ ድሴ "የአራት ሃይማኖት ካህን ሙሴ የተባለ የደንቢያ ሰው ተባባሪያቸው ነበር" በማለት እየተረጎሙ አንብበውልኛል::

1ኛ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ 2ኛ ዕጨጌ ወልደ ማርያም
3ኛ መምህር አካለወልድ 4ኛ ሸህ ሁሴን ጅብሪል::
5ኛ የአራት ካህን ሙሴ ሌሎችም ምሁራን ነበሩ::

አጤ ቴዎድሮስ ካህን ቢጠሉም በሄዱበት ሁሉ ጽላትና ሥዕል ካህናትና ዲያቆናት ሳያቢዙ አይሄዱም ነበር:: አብረው የሚሄዱ ካህናትና ዲያቆናትና ካህናት መካከል::

1ኛ ቄስ አለሙ 2ኛ ቄስ ካሣ 3ኛ ቄስ ታፈረ

ካበቃቸው ምክንያት አንዱ ምናልባት የሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጦራቸው የማይደፈር ስለሆነ ቴዎድሮስ እዚያ ተሸንፈው ወይም ደክመው ሲመለሱ እኔ ከዚያ የጎጃምን ጦር ይዤ የደከመውን ጉልበታቸውን ባዲስ ጉልበት ተቀብዬ አሸንፈዋለሁ የማለት ተስፋ ይሆናል" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ተድላ ጓሉ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ መሸፈታቸውና አጤ ቴዎድሮስ እልህ አስጨራሽ ጦርነት እንዲያደርጉ አስገድደዋቸዋል። አጤ ቴዎድሮስም ተከታትለው ተራራ ለተራራ ሲያናውጿቸው ኑረዋል። አጤ ቴዎድሮስ ደጃዝማች ተድላ ጓሉን ለመቅጣት ሲሉ አልባሌ ሰው ሁነው ከሕዝብ መካከል ገብተው ወሬ እስከመሰብሰብ ደርሰው ነበር። በደጃዝማች ተድላ ጓሉ ምክንያት ያለፈላት መነኩሲ ነበረች። ከላይ እንደተባለው አጤ ቴዎድሮስ ከሸዋ ወደ ጎጃም ሲመለሱ ደጃዝማች ተድላ ጋር ጦርነት ከፈቱ።

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 101 "አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን ወግተው ወደ ጎንደር ለመመለስ ዓባይን ሲሻገሩ ተድላ ጓሉ ከመንቆረር ወጥተው ከምሽጋቸው ገቡ ቴዎድሮስም ጅብላንብሬ ተድላ ጓሉን ሳልይዝ አልሄድም ብለው መንቀረር ላይ ሠፈር አደረጉ። የጅብላ ምሽግም ባለመስበሩ ቴዎድሮስ በአገሩ ላይ ራስ እንግዳን ሹመው ጎንደር ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ተድላ ጓሉ አጤ ቴዎድሮስ ሲሄዱባቸው አንዴ ተራራ ላይ በሌላ ጊዜ ደግሞ በርሃ እየገቡ ሲያስቸግሩ ኑረው በኅዳር 6 ቀን 1860 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት አስቀድመው እርሳቸው ሞቱ። በወሎ ደጃዝማች ዋግሹም ጎበዜና ደጃዝማች አመዴ በሽር፣ ወይዘሮ መስታይትና ወይዘሮ ወርቂት፣ሌሎችም መኳንንቶች ለአጤ ቴዎድሮስ አንገዛም ብለው ብዙ ጊዜ ጦርነት ገጥመዋል።

በተለይም ደጃዝማች አመዴ በሽር፣አጤ ቴዎድሮስን ካሰቃዩአቸው መኳንንቶች መካከል አንዱ ናቸው። ደጃዝማች አመዴ በሽር፣ አጤ ቴዎድሮስ ሲደርሱ በቅጽበት እልም ይላሉ፣አጤ ቴዎድሮስ ሰላም ነው ብለው ሕዝቡን ቀጥተው ሲመለሱ ደጃዝማች አመዴ በሽር ከተደበቁበት ወጥተው ይመጣሉ። በደጃዝማች አመዴ በሽር ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ ወሎን ቅጥቅጥ አድርገውታል።



ደጃዝማች አመዴ በሽር ወሎን የተለያዩ አውራጃዎችና ወረዳዎችን ሳይቀር እየዞሩ በአጤ ቴዎድሮስ እንዲመቱ አድርገዋል። አጤ ቴዎድሮስ ደግሞ አስቀድመው ያወጡት አዋጅ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ስለፈለጉ በደረሱበት አውራጃና ወረዳ ውስጥ ፍትሐ ነገሥት ተገልጦ ሕግን የሚያውቁ ሊቆች ወስነው የተማረከው ምርኮኛ ሁሉ እንዲገደል ያደርጋሉ።

<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው</u> አንበሳ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 128 "አጤ ቴዎድሮስ በኅዳር ወር አገሩ ሁሉ በሽር አመዴን እየረዳ ስለአስቸገራቸው ከጉራምባ ጀምሮ እስከ ገነቴና እስከ ጨለቃ ወንዝ እስከ ሸዋ ደንበር ያለው አገር ሁሉ እንዲመታ አድርገው ብዙ ሕዝብ አለቀ፣ ብዙ ንብረት ተዘረፈ። በወረራው ሽብር በየመንደሩ ወድቀው ሲንገላቱ የተገኙትን ሕፃናት አሰባስበው ለመኳንንቶቻቸው እያደጉ እያሉ ሰጥተዋል" ይሉና።

ገጽ 136 "አመዴ በሽር እንደተለመደው ሸሽቶ ሲያመልጥ ደጃዝማች ትኩ ብርሌን ግን ሁለቱ ልጆቻቸው ጦርነት ገጥመዋቸው ሲዋጉ አንዱ ልጃቸው በጦር ወግቶ ማረካቸው። ወዲያውም አባታችንን ወግተን ማርከናቸዋል ሲሉ ለንጉሡ ነገሥቱ የምሥራች ልከውላቸዋል። አጤ ቴዎድሮስም ከወላጅ አባታቸው እኛን ቢወዱ አይደለም ወይ እንደዚህ ያለ ጀብድ መሥራታቸው በማለት ከተደነቁና ከአመሰገኑ በኋላ ግዛቱን ለሁለቱ ወንድማማቾች አካፍለው ሰጥተዋቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ወቅቱ አንድነት የሚፈልግና አንድነትን የማይፈልግበት ዘመን በመሆኑ ከአባታቸው ጋር እስከ መዋጋት ደርሰዋል። አጤ ቴዎድሮስ በእንዲህ ባለው ወቅት የማረኩትን ሕዝብ ቢገድሉ በእውነቱ ተጠያቂው ማን ሊሆን ነው? ይህን የሕዝብ እልቂት እንዲደርስበት ያደረጉት እንደ ደጃዝማች አመዴ በሽር ዓይነት መሳፍንትና መኳንንቶች ናቸው።

ደጃዝማች አመዴ በሽር ባይሸፍቱና ሕዝቡን ከእርሳቸው ጋር ባያሳምጹት ኑሮ ይህ ቅንና ደግ ሕዝብ በአጤ ቴዎድሮስ ስቃይ አይደርስበትም ነበር። እንኳን ቀደም ዛሬም ቢሆን አንዳንድ አፈ ጮሌዎች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሕዝቡን ማሳመጽ ተግባራቸው

ሆኖአል:: እነዚህ በዘመነ መሳፍንት ወቅት የነበሩት መኳንንቶች ደግሞ በሽፍትነት የዳበሩ ነበሩ:: ለዚህ ሲሉ ሕዝቡን ቀስቅሰውና አሰነሥተው ጦርነት ሲገጥሙ የሚያልቀው ሕዝቡ ነው::

ጦርነት በሚደረግበት አካባቢ ሁሌም ሕዝቡን ይጎዳል:: ይህ ጸሐፊ በ1971 ዓም አርማጭሆ 21 ቀን ሙሉ የተመለከተውን ጦርነት አይረሳውም:: በዚህ ጦርነት የሁለት ወረዳ ሕዝብ ሲሰደድና ተባራሪ ጥይት ሲመታው ተመልክቷል:: የደርግ ጦር ቤቱን ሲያቃጥለው እህሉ አብሮ ተበልቷል::

ሕዝቡ የቅጠል ጎጆ ሠርቶ በብርድና በዝናብ ከርሟል:: ይህን ያደረጉት ድርጅቶች ሲጠቁ ወደ ሱዳን ሄዱ:: ሕዝቡ ግን ከሞት የተረፈው ችግሩን ሲጋፈጥ ከረመ:: በአጤ ቴዎድሮስም ዘመን የዚህ ዓይነት ችግር በሕዝቡ ላይ እንደደረሰበት ማገናዘብ ይቻላል:: ታዲያ ይህን ሕዝብ ያስጨረሱት መኳንንቶች ራሳቸው ናቸው ማለት ይቻላል:: አጤ ቴዎድሮስ ከወሎ ወደ ሸዋ ዘመቱ:: ምክንያቱም አቶ ሰይፉ በመሸፈታቸው ምክንያት እርሳቸውን ለማስገበር ሄዱ::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 138 "አጤ ቴዎድሮስ የአቶ ሰይፉን መሸፈት ስለሰሙ ልጃቸውን ደጃዝማች መሸሻን ራስ ሙቤን አቡኑን ዕጨጌውን ካህናቱን የአደባባይ ኢየሱስን የግምጃቤት ማርያምን ጽላት የያዙትን ሥዕል ቤቶችን በጠቅላላው የቤተመንግሥቱን ዕቃና ግዝ መቅደላ አምባ ውስጥ አግብተው ደረቅ ጦር ሁነው በ1852 ወደሸዋ ገሥገሡ ሰላ ድንጋይ በደረሱ ጊዜ ወታደር ሳይታዘዝ አገር በመዝረፉ ሠላሳ ሰባት ወታደሮች እጅ እግራቸውን አጥተዋል:: ከተንታ በተነሡ በስምንት ቀን አንኮበር ደረሱ::"

"ከዚህም ላይ ጥቅምት ሁለት ቀን በተደረገው ጦርነት ከንጉሡ ወገን የጦር አለቃ ተማርኮ ወደ አቶ ሰይፉ ቀረበ እርሳቸውም ይህ አሁን የሚዋጋው ጦር የማን ነው አንተስ የማን ነህ ብለው ጠየቁት ምርኮኛውም እንዴት አላወቁትም አጤ ቴዎድሮስ ናቸው እኮ ብሎ በነገራቸው ጊዜ ጦርነቱን አቋርጠው ሠራዊታቸው ሳይሰማ በስውር ሸሹ ጦሩ ግን ከጧት የጀመረ እስከጨለማ ድረስ አላስገባም በማለት በቅጥር ውስጥ እንዳለ ሆኖ የሰይፉን መሸሽ የማያውቅ ወታደራቸው ጃንሆይ ጃንሆይ እያለ ሲጮህ አጤ ቴዎድሮስ ሰምተው ሠራዊቱን



ግዛቡት እያሉ በማደፋፈር ወደፊት ስለገፋበት ቅጥሩን እያፈረሰ ገባበትና የአንኮበር ጦርነት በዚህ ዓይነት ተፈጸመ" ሲሉ ጽፈዋል::

እንዲህ ባለ ጦርነት ድል አድርገው አደላድለው ቢመለሱም ሸዋ ከመሸፈት አልዳነም:: ከዚያም በኋላ በ1857 ዓም አጤ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ከትውልድ አገራቸው ሲገቡ ተከታዮቻቸውን አብዝተው ነበሩ::

በጎንደር ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ፤ የወልቃይት ተወላጅ ናቸው:: አልገብርም ብለው በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ሸፈቱ:: አጤ ቴዎድሮስም እንደ ደጃዝማች አመዴ በሽርና እንደ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ጠንክረው ባይዘምቱባቸውም በተደጋጋሚ ደብድበዋቸዋል:: ነገር ግን እንኳን ያኔ ዛሬም ቢሆን ወልቃይት ጠገዴ በርሃው ከባድ በመሆኑ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ አጤ ቴዎድሮስን ሊያመልጡ ችለዋል::

ውሎ አድረው የአጤ ቴዎድሮስ ኃይል እየቀነሰ እርሳቸው ሙሉ በሙሉ ፊታቸውን ወደ እንግሊዝ ጦር ሲያዞሩ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ጎንደርን ይዘው ፊታቸውን ወደ ወሎ አዙረው ነበር:: ከዚህ ላይ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜን እንግሊዞች መሸፈታቸውን ማወቃቸው እንጂ ደብዳቤ ይላኩላቸው አይላኩላቸው የሚያብራራ ሰነድ ሊገኝ አልቻለም:: በእንግሊዞች ግን መታወቃቸው አልቀረም:: ያም ሆነ ይህ ደጃዝማች ጥሶ ጎበዜ ለመንገሥ ጥረት አድርገዋል:: ባልታሰበ ሰዓት ደጃዝማች ዋግ ሹም ጎበዜ፤ በለሳ ላይ ሚያዝያ 1860 ዓም ወግተው ገደሏቸው::

<u>ሐሌፍ መጽሔት</u> ቁ 1 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 18"አንዳንዶቹ የሥልጣን ርክክቦሽ ጦርነቶች አጭር አንዳንዶቹም ረዥም ናቸው:: በጣም ወደኋላ መሄዱን ትተን የዘመነ መሳፍንትን ፍጻሜ ለማምጣት ከተደረገው ጀምሮ ያለውን በምሳሌነት እንይ! የዘመነ መሳፍንትን አገዛዝ አስወግዶ አንድ ኢትዮጵያና ማዕከላዊ መንግሥት እንደገና ለማምጣትና ለማጠናከር መይሳው ካሣ አጤ ቴዎድሮስ ከመባላቸው በፊት ጀምሮ እስከ ለተ ሞታቸው ድረስ ጦርነት ያላካሄዱበት ዓመት አልነበረም:: በተለይም በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረው ጦርነት ከባድ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

ደጃዝማች ካሣ ምርጫ የኋላው አጤ ዮሐንስ ሥልጣን ለማግኘት ሲሉ አገራቸውን ያስወረሩ ከደጃዝማች ንጉሤ ወልደ ሚካኤል ቀጥለው ዋና ተወቃሽ ናቸው:: እንግሊዞችም የእርሳቸውን ድጋፍ ባያገኙ ሌላው ቢቀር የእህል ችግር ስለሚያገኛቸው አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ እንኳን ረጋ ብለው የአገሪቱን ቅርሳቅርስ ለመዝረፍ ጊዜ አያገኙም ነበር:: ለዚህ ዋናው ተወቃሽ ለመሆናቸው ደጃዝማች ካሣ ምርጫ ከእንግሊዝ ጦር አዛዥ ጋር የተነሡት ምስል ፎቶ ዋቢ ምስክር ነው::

ዶ/ር ተወልደ ትኩእ <u>የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣሊያ</u> በቷባለው መጽሐፋቸው ገጽ 136 "የዋግሹም ጎበዜ እና የበዝብዝ ካሣን ምሳሌ በመከተል ምኒልክም ከመቅደላ ሸሽቶ ሸዋ ገብቶ ሥልጣን ለመያዝ በቅቶ ነበር:: እነዚህ ሁሉ ፀረ አጤ ቴዎድሮስ አመጸኞች ቴዎድሮስን ለመዋጋት ወደ ኢትዮጵያ የገባውን የእንግሊዝ ሠራዊት እንደነጻ አውጭ ነበር የተመለከቱት:: የቴዎድሮስን ፍጻሜም በደስታ ነበር የተቀበሉት:: አጤ ቴዎድሮስ በዘመነ መንግሥቱ በሕይወቱ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በውጭ ሀገር ዜጎች ጠላቶችን እንጂ ወዳጆችን አላፈራም" ሲሉ ጽፈዋል::

በእርግጥ "የእንግሊዝን ሠራዊት እንደነጻ አውጭ ነበር የተመለከቱት" ያሉት ሊቅ ተወልደ ደጃዝማች ካሣ ምርጫን እንጅ ሌሎችን አይመስለኝም:: ዋግሹም ደጃዝማች ጎበዜ በደብዳቤ ቢተባበሩም ከእንግሊዝ ጦር መሪ ጋር አልተገናኙምና የእንግሊዝን ጦር እንደ ነፃ አውጭ አልቆጠሩትም:: እንደ ነፃ አውጭ ቢቆጥሩትማ ኑሮ ጀኔራል ናፒር "ይምጡ"እያለ ሲልክባቸው መሄድ ይችሉ ነበር:: በእርግጥ አጤ ቴዎድሮስን አይወዱም ትክክል ነው:: ነገር ግን የእንግሊዝን ወታደር እንደ ነጻ አውጭ አልተመለከቱትም::

<u>ኢትዮጵያና ዕድሏ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 125 "በዝብዝ ካሣ ለአጤ ቴዎድሮስ ታማኝ ሆነው ቢቆዩም የቴዎድሮስ ውድቀት ዘመን ሲቃረብ ከእንግሊዞች ጋር ተስማምተው ከትግራይ ክፍለ ሀገር እስከ ምጽዋ ወደብ በሠራዊት ተጠናክረው ነበር:: የእንግሊዝ ጦር አጤ ቴዎድሮስን ለመዉጋት ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ካሳ መንገዱ እንዲቃና በማድረጋቸው የእንግሊዞችን ወዳጅነት ስላተረፉ ኋላ



ሥልጣን ለመያዝ እንዲችሉ የእንግሊዞችን እርዳታ ሙሉ ድጋፍ አግኝተዋል::"

"እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስን ለመውጋት ከምጽዋ እስከ መቅደላ ያለውን 650 ኪሎ ሜትር ለመጓዝ የበዝብዝ ካሳን ድጋፍ ባያገኙ ኖሮ በየመንገዱ ሕዝቡ ግጭትና መሰናክል ስለሚገጥማቸውና ምግብም ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ቴዎድሮስን ድል የማድረጉ ሁኔታ አጠራጣሪ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: ኮሎኔል አስራት ቦጋለ እንዳሉት ጥሩ ግምገማ ነው::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 366 "አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በተነሡበት ጊዜ ከውስጥ የተነሡባቸው መሳፍንትና ትናንሽ ነገሥታት ይህን ዓላማቸውን ሲቻላቸው በፊት ውጊያ ሲጨንቃቸው በሽፍትነት እያመፁባቸው የተረጋጋ መንግሥት እንዳይመሠርቱ አድርገዋቸው ነበር::"

"ይህ ሁሉ አልበቃ ያላቸው መሳፍንት በመጨረሻው አስተባብረው ያመጡት የእንግሊዛውያን ጦር ወደ መሀል አገር መግባት የቻለው በዚህ በር ነበር:: ቴዎድሮስ እጅ ሰጥቶ መማረክ ወይም በሽሽትና በስደት መሞት ታሪካቸውን እንደሚያጎድፈው ወታደሮቻቸውንም እንደሚያሸማቅቅ ስላወቁ ራሳቸውን ሠውተው አለፉ" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ልብነ ድንግል ሙተው ልጃቸው ደጃዝማች ገላውዴዎስ የአጤ ግራኝ አህመድን ጦር እየተዋጉ ነበሩ።

ኋላም ደጃዝማች ገላውዴዎስ ከወላጅ እናታቸው ከቴጌ ሰብለ ወንጌል መልእክት ሲደርሳቸው ወደ ትግራይ ተሻግረው ከዶም ክርስቶፎር ደጋማ፤ ጋር ተገናኝተው ተመካከሩ። ተባብረው አጤ ግራኝ አህመድን ጦርነት ገጠሙአቸው። ነገር ግን የአጤ ግራኝ አህመድ ጦር ከሐረር እስከ ባሕረ ነጋሽ እየጠረገ የመጣ ኃይለኛ በመሆኑ የማይቀመሳቸው ሆነ። በዚህ ወቅት የመጡት 400 ወታደሮች ከሁለት ቀን ጦርነት በኋላ ግማሾቹ ሲሞቱ ግማሾቹ ወደ መጡበት አገራቸው ተመለሱ።

ዶም ክርስቶፍ ደጋማ 20 የማይሞሉ ወታደሮችን ብቻ ይዘው ከደጃዝማች ገላውዴዎስ ጦር ጋር ሁነው ጡጊያውን ተያያዙት። ነገር ግን እርሳቸውም በአጤ ግራኝ አህመድ ጦር ተማረኩና ተገደሉ። በዚህ ወቅት በአንድ የከንባታ ጦረኛ አጤ ግራኝ አህመድ ሲቆስሉ የተመለከተ የፖርቱጋል ወታደር "እኔ መታሁት ግራኝን" ብሎ ለደጃዝማች ገላውዴዎስ ተናገረ።

አጤ ግራኝ አህመድ ቁስላቸው ጠንክሮባቸው ሞቱ። በዚህ ወቅት ደጃዝማች ገላውዴዎስ አጤ ሁነው በኢትዮጵያ ነገሡ። ያ የከምባታ ጦረኛ መሸለም ሲገባው አጤ ገላውዴዎስ ለአፈ ሙሌው ለፖርቱጋሉ ሰጡት። ከዚህ ወቅት ጀምሮ የፖርቱጋልና የኢትዮጵያ ግንኙነት ሲጀምር አውሮፓውያን ኢትዮጵያ የተባለች አገር መኖሯን ጠንቅቀው አወቁ።

ኋላማ በብዛት ፖርቱጋሎች ገቡና አጤ ሱስንዮስን አሳምነው የኢትዮጵያ የመንግሥት ሃይማኖት ካቶሊክ መሆን አለበት ብለው እንዲያውጁ አደረጉ። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጦርነት ወደ ጦርነት እንዲገባ አድርገዋል። ተዋሕዶ አማኞች በአንድ ቀን ብቻ 24 ሺህ ሰዎች ደንቀዝ ላይ ታርደዋል። ይህ ጦርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ በአጤ ግራኝ አህመድ ካለቀው ይልቅ ሕዝቡን አስጨረሰ። በዚህ ወቅት አጤ ሱስንዮስ ታመሙና ልሳናቸው ተዘጋ።

የካቶሊክ ካህናት በጸሎትና በጸበል ቢሞክሩ ለውጥ አላሳዩም። ታዲያ ደጃዝማች ፋሲል ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ላሉት አባቶች "አባቴ ታመዋል ኑና በጸሎታችሁ እርዱኝ" ብለው ላኩባቸው። የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አባቶችም ጎርጎራ ቤተ መንግሥት መጡና ጸሎትና ምህላ ሲያደርጉ ሰንብተው ጸበል ሲረጯቸው አጤ ሱስንዮስ "ሃይማኖት ይመለስ ፋሲል ይንገሥ" ብለው ተናገሩ።



ከዚህ ወዲህ ተዋሕዶ ሃይማኖት ነፃ ስትወጣ ካቶሊኮች ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ በአጤ ፋሲል ሲታዘዙ ብዙዎቹ ወደ ሀገራቸው ሄዱ። ነገር ግን አንዱ ተንኮለኛ የካቶሊክ መነኩሴ አድዋ ሲደርስ "አሞኛል" ብሎ ተኛ። ከዚህ ቦታ ላይ የካቶሊክን ሃይማኖት መሥርቷል። ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን የሚያፈርሱ አንዳንድ ግለሰቦች የሚወለዱበት ቦታ ይህ አድዋ ሆነ።

ከዚህ ወቅት ጀምሮ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን በገናናነትና በሃይማኖት ክርስቲያን መሆንዋን ጠንቅቀው አወቁ። የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ)ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቆች ከኢየሩሳሌም ወደ አውሮፓ ገብተው ሃይማኖትንና የግእዝን ፊደል የአማርኛን ቋንቋ አስተምረዋል። በተለይም አባ ጎርጎርዮስ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ሁለት ታላላቅ መጻሕፍትን ይዘው መላ አውሮፓን ዞሩ።

አባ ጎርጎሬዮስ ወደ አውሮፓ የሄዱበት ዘመን በ1640 ዓም ሲሆን ለኢትዮጵያ ታሪክና ለተዋሕዶ ሃይማኖት ምሰሶ ሁነዋል። እርሳቸው ምንም እንኳ የተዋሕዶን ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መሥርተው ማስተማር ባይችሉም የሃይማኖቱን መሠረትና ሥርዓት የግእዝን ኃያልነት ለአውሮፓ ምሁራን አስተምረዋል። ለዚህም ነው ዛሬ ድረስ ጀርመን አገር በዩንቨርስቲ ደረጃ የግእዘ ትምህርት የሚሰጠው።

ለምሳሌ አባ ጎርጎርዮች ጀርመን አገር ከ12 ዓመት በታች ያሉትን ሕፃናት ሰብስበው ግእዝ እና አማርኛ ቋንቋ አስተማሩአቸው። እነዚህ እርሳቸው ካስተማሯቸው መካከል ሉድፍ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። ዶልፍ ብዙ መጻሕፍትን በግእዝ እና በአማርኛ ቋንቋ ጽፈዋል። ለምሳሌ እነዚህ መጻሕፍት የታተሙበትን ዘመን ተመልከቱ።

1ኛ ግእዝ ሰዋሰው በ1661   2ኛ ግእዝ ላቲን መዝገበ ቃላት
3ኛ አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ  4ኛ የኢትዮጵያ ታሪክ 1698

ግን በቆንስል ደረጃ የተቀመጡ ባይሆኑም የአጤ ቴዎድሮስ ወታደር ነበሩ ማለት ይቻላል። ለዚህም ነው ሊቀ መኳስ ያሏቸው አጤ ቴዎድሮስ፤ እነዚህ ሁለት እንግሊዞች አጤ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያጠነክሩ ባላቸው ችሎታ ሁሉ አስረዷቸው።

አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ያን ያህል ይጠሉት የነበረውን ፕላውዴን የወንድማቸው ልጅ በመግደሉ ምክንያት ማዘን ብቻ ሳይሆን ተበሳጭተዋል። ይህ የአጤ ቴዎድሮስ ጸባይ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ ጸባይ ነው። ይከደኛል ብለው ሳይጠረጥሩ ከልባቸው ነበር የወደዱት። ፕላውዴም ለአገሩ መንግሥት ድጋፍ እቅዳቸውን ዘርዝሮ ከመጻፍ አልተቆጠበም ነበር።

ቆንሲል ፕላውዴን ኑሮ ቢሆን አውሮፓውያን በአጤ ቴዎድሮስ አይታሰሩም ነበር። የእንግሊዝ መንግሥትም ያን ያህል ወጭ እያወጣም ነበር። ጦርም አያዘምትም ነበር። በቆንስል ፕላውዴን ቦታ ጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን መምጣቱና የኢትዮጵያ እና የእንግሊዝ መንግሥት ግጭት ከዚህ ዝቅ ብሎ ባለው ምዕራፍ ይቀጥላል።

## ምዕራፍ 3

### የጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን መምጣትና መታሰር!

በአጤ ቴዎድሮስ የተጻፈ ደብዳቤ እንግሊዝ አገር ሲደርስ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ካሜሮን የሚባል ጉዳይ ፈጻሚ ወደ ኢትዮጵያ ይልካል። አጤ ቴዎድሮስ ካሜሮንን እንደ ፕላውዴ በማየት የልባቸውን ስሜት ሳይደብቁ ነገሩት። ፍላጎታቸው በኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ማምረት ሲሆን ለዚህ ቅዱስ ዓላማ አስተማሪ ከእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ጠየቁ ይህ ብቻ ሳይሆን ቱርኮችን አስመልክቶ ሌሎች ጉዳዮችን ሳይቀር ነግረው ገንዘብ ሰጥተው ለደብዳቤያቸው መልስ ይዞ እንዲመጣ ላኩት።

ቆንስል ካሜሮን በሰላም አጤ ቴዎድሮስን ተሰናብቶ ወደ ምጽዋ ሄደ። ከዚያም አጤ ቴዎድሮስ የሰጡትን ደብዳቤ በፖስታ ልኮ እርሱ ወደ ከሰላ ተመልሶ ከቱርክኮች ጋር ሲገባበዝ ሲከርም ለፈረንሳይ



መንግሥት ደብዳቤ አሲዘው የላኩት ሰው ደብዳቤውን አድርሶ ጎንደር ሲገባ ቆንስል ካሜሮን ግን ደብዳቤው ይድረስ አይድረስ እንኳን ሳያጣራ ወደ አጤ ቴዎድሮስ ሠፈር መጣ። አጤ ቴዎድሮስ ቆንስል ካሜሮንን ከእንግሊዝ አገር አጅበውት የሚመጡ የእጅ ባለሞያዎች ናቸው ብለው ሲጠብቁ፤ እርሱ ግን ከቱርኮች ጋር ሁኖ ሲያማቸውና በሕዝባቸው ላይ ሲቀልዱባቸው መሰንበቱን ቀደም ብሎ የደረሳቸውን ወሬ የሚያጠናክር ሆነ።

እንዲያው አጤ ቴዎድሮስ "ለደብዳቤዬ መልስ አመጣህልኝ ወይ" ሲሉት ቆንስል ካሜሮን ግን "አላውቅም" ሲላቸው አጤ ቴዎድሮስ ተቆጡ። አስተርጓሚው ግን ለአጤ ቴዎድሮስ አስቀድሞ መልእክት መላኩ ታውቋል። ይህ ብቻ ሳይሆን አስተርጓሚው አቶ እንግዳ ወርቅ፤ የኢትዮጵያን ባህላዊ ቀረርቶና ፍከራ እንዲፈክሩ በጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን ታዘዙ። አቶ እንግዳ ወርቅ፤ ጥሩ ገጣሚና አቀንቃኝ መሆናቸው ግጥሙ ይመሰክራል።

"ጃሎ በሉ፤መገን፤ በሉ ጎራው በሉ፤ጀግና በሉ
ይርቀን እንደሆን ምቀኛችን፤ በሽታችን ሁሉ፤
ጃሉ በሉ ጎራው በሉ ያቀምስሃል ያሰው እጁን እንዳመሉ"

በማለት አቶ እንግዳ ወርቅ፤ አቅራርተዋል። ይህን ከዚህ በላይ ያለውን ግጥም ዛሬ ካሉት ባህላዊ ድምጻውያን መካከል ድምጻዊ ወረታው ውበቴ፤ ትንፋሹን አምቆ በመስንቆ ቢያጉረመርመው ስንቱ ይሸንጠው ነበር። ጃሎ ብለው የደረደሯቸው ግጥሞች ቱርኮች የቋንቋው ምሥጢሩ ስላልገባቸው እንጂ እነሱንም ጭምር የሚነቅፍ ለመሆኑ "ያቀምስሃል ያሰው እጁን እንዳመሉ" ያሉት ቀደም ሲል አጤ ቴዎድሮስ ቱርኮችን መደብደባቸውን የሚገልጽ ሲሆን ጃሎታቸውን ካሰሙአቸው በኋላ ደግሞ ከዚህ በታች ያለውን ፎክረዋል።

"ዘራፍ ቆፍጣናው ዘራፍ የዛለት
ዘራፍ የዛ ለት ደፋር ከፈሪ የተለየለት
አባሮ ገዳይ በአባቱ መሬት
አልሞ ተኳሽ የማይሳሳት
ወዳጅ ሲመስል ጠላት ሆነበት
የበላበትን ሰባሪ ወጭት

አጤ ቴዎድሮስን አገር አፍቃሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይወዳቸዋል:: ሕዝቡ የዚህ ጎሳ የዚህ አማኝ ሳይባል ይኮራባቸዋል:: ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ወደ ወንበሩ ብቅ የሚሉ ባለሥልጣኖች አጤ ቴዎድሮስን አይወዷቸውም:: በእርግጥ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይወዷቸው ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን" አውሮፓውያን ለእርስዎ መታሰቢያ ሐውልት እንሥራ" ሲሏቸው የመለሱላቸው መልስ "እኔ ለሀገሬ የሠራሁት ሥራ የለም::

ለሀገሬ የሠሩት አባቶቼ አጤ ቴዎድሮስና አጤ ዮሐንስ፣ወላጅ አባቴ አጤ ምኒልክ ናቸው የምትሠሩልኝ ከሆነ የአጤ ምኒልክን ሥሩልኝ" ስላሉ አራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ቆሞ የሚታየው ሐውልት ተሠርቶ ሳይመረቅ እርሳቸውን ገደሉአቸው:: ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለአጤ ቴዎድሮስ ፍቅር ነበራቸው:: ለምሳሌ ሶማሌ ኢትዮጵያን ስትወር አገር ለመከላከል የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥሪ ሲያቀርቡ ሕዝቡ ጥሪዉን ተቀብሎ ሲሄድ ማሰልጠኛ ጣቢያው ታጠቅ ተብሎ ነበር የተሰየመው::

ወራሪን መልሰው በውስጡ ችግር ተጠምደው ሳለ አጤ ቴዎድሮስ መድፍ ባሠሩበት ጋፋት በሚል ስያሜ ኩባንያ ከፈቱ:: ይህ ኩባንያ ለአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጭ ገቢያ ይውልላል ተብሎ ታስቦ ነበር:: ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጻፉት መጽሐፍ በቅርቡ እንደሚወጣ አውቃለሁ::

ታዲያ ከዚህ መጽሐፍ አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የጻፉት መልካም ነው:: አጤ ቴዎድሮስ ሕዝቡና መኳንንቱ አልከተላቸው ብሎ እንጂ አገሪቱን ለማሳደግ የነበራቸውን ጅመራ አድንቀው መጻፋቸውን ሰምቻለሁ:: በትረ ሥልጣን ከጨበጡት መካከል ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለአጤ ቴዎድሮስ የላቀ ክብር አላቸው:: አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና ገጣሚዎች፤ ሠዓሊዎች፤ ድምጻውያን ዘንድም ከፍተኛ የሆነ ፍቅር ዓላቸው::

ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ማንንም አይወዱም ነበር:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሙተው እየተለቀሰ ባለበት ወቅት በታሪክ የመጀመሪያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ አብርሃም ምርር ብለው



ሲያለቅሱ አቡነ ሚካኤል "ተረጋጉ"እያሉ ሲያጽናኑአቸው "ኢትዮጵያ ሰው አጣች" ሲሉ ጃንሆይ ይሰማሉ::

ታዲያ ጃንሆይ ቆጣ ብለው "እንዴት ኢትዮጵያ ሰው ታጣለች እኛ እያለንላት" ሲሉአቸው አቡነ አብርሃም "አዎ ኢትዮጵያ ሰው አጣች ገዳይዋ በዝቶ" ሲሉ መለሱላቸው በዚህ ምክንያት አታካሮ ገብተው ሳይታረቁ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ስትወር አቡነ አብርሃም ጣልያንን ደገፉ:: ከጣልያን ጋር ባሉ መኳንንቶች ጥረት የመጀመሪያው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆኑ::

ጃንሆይ ከእርሳቸው በላይ ሌላ ለኢትዮጵያ የሠራ መስሎ አይታያቸውም ነበር:: በዚህ ምክንያት የአዲስ አበባን መንገዶች በውጭ አገር ሰው ስም ከምንሰይም በአባቶቻችን ስም ይሰየሙ ብለው የተከራረከሩ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይዎት ናቸው:: ምንም እንኳን ቢትወደድ የሕይወት ውጣ ውረድ በተባለው መጽሐፋቸው ላይ ባይጠቅሱትም ሎስ አንጀለስ ሳሉ ሲጫወቱ ሰምቻቸዋለሁ:: ምናልባት ክፍል ሁለት መጽሐፋቸው ገልጸውት ከሆነ ልጃቸው ሲያሳትሙት እናነባለን አለበለዚያ ደግሞ ተሰርዟል ማለት ነው::

ሊቀ ጠበብት ኃይሌ ገርማ አድዋ በተባለው ተውኔት ፊልም ላይ ከአዲስ አበባ ጉዞ ወደ አድዋ ሲያደርጉ ወሉ ደሴ ከተማ መግቢያ ላይ በትልቁ የአጤ ቴዎድሮስ ምስል የተሳለዉን ቀርጸው ያሳዩታል:: ባሕር ዳር ድብ አንበሳ ሆቴል በር ላይ የተሠራውን ሐውልት እኔ ራሴ አይቸዋለሁ:: በጎጃም ክፍለ ሀገር በአገው ምድር አውራጃም በስማቸው "ቴዎድሮስ አንድነት ገዳም"የሚባል መኖሩን ሰምቻለሁ::

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ አርቀው በሚያስቡ ታሪክ በሚያከብሩ በቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወትና በአንዳንድ የሸዋ አባቶች ጥረት የተመሠረተው ሐውልት ብዙም ሞቅ ያላለ ሲሆን በወያኔ ኢሕአዴግ ዘመን የተሻሻለ ቢመስልም የሚታየው መድፉ እንጂ የአጤ ቴዎድሮስ ሥዕል የለም::

ይህንም ያሠሩት የባድሜ ጦርነት ወራት በመሆኑ ሕዝቡ ስለ አንድነት ይዘምር ስለነበር ሕዝቡ የሚወደውን መውደድ ስላለባቸው እንጂ የአጤ ቴዎድሮስን ሐውልት ለማሠራት ፍላጎቱ ኑሮአቸው

# ክፍል አሥራ ሁለት

## ምዕራፍ 1

### አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አይደሉም?

በዘመነ ኢሕአዴግ ብዛት ያላቸው ቡድኖች አጤ ቴዎድሮስን አጥላልተው መጽሐፍ መጻፍና በቴፕ ክር ማስቀረጽ በዝቷል። ሕወሓት በርሃ ሲንቀሳቀስ ሳለ ጀምሮ እስላሞችን "ተበድላችኋል፣ ጊዜው አሁን ነው። አክሱም መስጊድ እንዳትሠሩ እኒህ ትምክህተኞች ከለከሏችሁ። የአማራው የገዥ መደብ በእስላም ኅብረተሰብ ላይ በደል አድርሷል"እያለ ቅስቀሳ ያደርግ ነበር።

በብዛት ከእስላሞች ሰፈር ብቅ እያሉ ይሰብኩ የነበሩት ጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ። ኢሕአዴግ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባ ከያዘ ጀምሮ ቂም በኢትዮጵያውያን ላይ እንዲዘራ አድርጓል እርሱ የዘራውን መርዝ ደግሞ የጎሳ አባላት ሆኑ የሃይማኖት መሪዎች ጥላቻቸውን ይዘው በአደባባይ ወጡ። ከነዚህም ሐጂ መሐመድ ወሌ አንዱ ናቸው።

ሐጂ መሐመድ ወሌ <u>እስልምናና የኢትዮጵያ ታሪክ</u> 14ኛ በተባለ ቴፕ ክር "ብንረሳ ብንረሳ አጤ ቴዎድሮስ በእስላሞች ላይ ያደረገውን ጭካኔ አንረሳም። አጤ ቴዎድሮስ በወሎ እስላሞች ላይ ጨክኖባቸው ነበር። እጅና እግራቸውን ቆርጦ መቅደላ ከሚባል ተራራ ላይ አስሮአቸው ነበር" ሲሉ አሰራጭተዋል።

አጤ ዮሐንስ ክርስትና ተነሡ ማለታቸው ግልጽ ነው። አጤ ምኒልክ ግን የተሰደቡበት ውሸት ነው። አጤ ኃይለ ሥላሴ የተወቀሱበት ሀሰት ነው። የሚገርመው ታሪክ ደግሞ "ጣልያን ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ዲሞክራሲ አግኝተን ነበር። ጣልያን ድሪዳዋ ላይ በኃይለ ሥላሴ የታሰሩ 20 ሺህ እስላሞች ተገኙ" ይላል ክሩ። ደርግም እንዲሁ ተወንጅሏል። ሐጂው ሲያክሉ "የአንበሳ ልጅ አንበሳ፣የነብር



ልጅ ነብር፣የጊንጥ ልጅ ጊንጥ ነው። ዛሬም እስላሞች አንድ ሁነን ለመብታችን መታገል አለብን" አሉ።

መናገርና መጻፍ ተፈቅዷል ቢባልም እንኳ ሀሰት መጻፍና መናገር ትክክል አይደለም። ሐጅ መሆን እኮ የሃይማኖት አስተማሪ መሆኑ ይመስለኛል። ሐጂ መሐመድ ወሌ ግን ሐሰት ተናገሩ። አባባላቸው "ቴዎድሮስ ራሱን ገደለ ይባላል። በእኛ ታሪክ ደግሞ የገደለችው ሴት ናት የመሐመድ ልጅ" ብለዋል።

አጤ ቴዎድሮስ በሞቱበት ሰዓት እንኳን ሌላ ሴት ወታደር በአካባቢው አልነበረም። የባለቤታቸው እናትና ባለቤታቸው እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤና ወይዘሮ ምንትዋብ የእንግሊዝ ወታደር የገደላቸው ሕጻኑ ዓለማየሁ ብቻ ናቸው። የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ለመበረዝ ሆን ተብሎ ከሆን በታሪክ የሚናቁት ሐጂ መሐመድ ወሌ ናቸው።

አጤ ቴዎድሮስ ሰኞ ዐርፈው ማክሰኞ ወደ ጄኔራል ናፒዬር ሰፈር የሄዱት ወይዘሮ መስታውት መሆናቸው የተመዘገበ መሆኑ አይካድም። በሐጂ መሐመድ ወሌ የቀረቡት የታሪክ ክሮች ሁሉም የጥላቻና የሀሰት ናቸው። ታሪክና ጥላቻ አብሮ አይሄድም። ይህን ቅድሚያ ሐጂ መሐመድ ወሌ ማወቅ ይገባቸዋል።

የእርሳቸውን ዓይነት የጥላቻ ቅስቀሳ የተቀበሉ ግለሰቦች ክርስቲያኖችን ማረዳቸው ግልጽ ሲሆን ሃይማኖት ያለው ሰው ደግሞ ሀሰት አይናገርም። በሰው ደም መፍሰስ ደስ የሚለውም ሰው ሊባል አይችልም። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ሲሆን አንዱ አንዱን እንዳይገድለው መከልከል ሲገባ ያልሆነ ታሪክ ማቅረቡ ለወደፊቱ ሊገታ ይገባዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አልነበሩም። ፀረ እስላም ቢሆኑማ ኑሮ ይህን ሕግ ሊያወጡ አይችሉም ነበር። "ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ፥እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ እንዲቀመጥ፥ ነገር ግን ክርስቲያን ከአንድ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፥ቢገኝ እስላሙም ከእስልምና ሃይማኖት ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ሲያስተምር ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪውም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፥ደረቱም በጦር ይወጋል" ሲሉ አውጀዋል።

